# የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞች የመረጃ ልውውጥ ማሰልጠኛ ማንዋል

## በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት የታተመ

ነሀሴ 2013 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ</u>

Feteh (Justice) Activity
IN ETHIOPIA

ይህ ህትመት በዩ ኤስ አሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) በአሜሪካ ህዝብ ድጋፍ በኩል መከናወን ተችሏል። በሰነዱ የተገለጸ ይዘት እና ሀሳብ ወይም አመለካከት በማንኛውም መንገድ የ ዩ ኤስ አሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ አመለካከትን አያንጸባርቅም።

# መቅድም

የኢትዮጵየ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት መጋቢት 16 ቀን 2018 የተመዘገበ የ17 ሀገር በቀል የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጥምረት ሲሆን፣ በምዝገባ ቁጥር 3932፣ በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት ምዝገባውን አድሶ የሚንቀሳቀስ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው፡፡ ኢሰመድህ በሀገሪቱ ውስጥ በዲሞክራሲ እና በሰብዓዊ መብቶች እንዲሁም በሰላም ግንባታ ውስጥ በመሳተፍ፣ ሰብዓዊ መብት ላይ ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማህበር ነው። ኢሰመድህ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሰብዓዊ መብት ማህበራት በጋራ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እና በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሙግት እንዲያካሂዱ የጋራ መድረክ በመፍጠር በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጥበቃን ለማሳደግ እየሰራ የሚገኝ ነው። ኢሰመድህ በሰብዓዊ መብቶች ላይ ለሚሰሩ ድርጅቶች ለመስራት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እና ውጤታማ የሰብአዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ሥራዎችን ለማረጋገጥ ከባለድርሻ አካላት ጋር የነባር እና አዳዲስ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚሰራ ድርጅት ነው። በዚህ ረገድ ኢሰመድህ ማንዋሎችን እና መመሪያዎችን በማዘጋጀትና ሥልጠናዎችን በመስጠት የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶችን፣ የሚዲያዎችንና ጋዜጠኞችን አቅም ለመገንባት ይተጋል፡፡

ህብረቱ ሚዲያዎች/ጋዜጠኞች የፍርድ ቤት ጉዳዮችን እንዲከታተሉ፣ እንዲመዘግቡ እና ሪፖርት እንዲያደርጉ እና በዳኝነትና በፍትህ ስርአቱ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን ለህዝቡ በማሳወቅ እና የህዝቡን ግንዛቤ በፍትህ ስርአቱ ላይ ለማሳደግ እንዲሁም የዜጎች የመረጃ ተደራሽነትን በተከታታይ እና በጥራት ለማሳደግ ይሰራል። ኢሰመድህ የFeteh (Justice) Activity - USAID ይህንን ማንዋል በ4 (አራት) ቋንቋዎች እንዲተረጎምና ለህትመት እንዲበቃ ላደረጉት የገንዘብ ድጋፍ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

መስዑድ ገበየሁ፣ ሥራ አስኪያጅ፣

የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ)

---

## ሕትመቱን በተመለከተ

---

***ይህ ህትመት የተዘጋጀው በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት (ኢሰመድህ) እና በዩ ኤስ አሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) ድጋፍ ነው።***

***ሰነዱን ያዘጋጀው፤ መስፍን ጫኔ ይመር***

***ሰነዱ የታተመው፤ ነሐሴ 2013 ዓ.ም***

***የዚህ ህትመት ቅጂ ሙሉ መብት የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት (ኢሰመድህ) ሲሆን ያለድርጅቱ ፈቃድ ይህን ሰነድ ማባዛት እና ማሰራጨት አይቻልም።***

## መግቢያ

ኢትዮጵያ እንደ ብዙዎቹ የዓለማችን አገራት የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራም በመቅረጽ በየጊዜዉ ከነውስንነቱም ቢሆን ተግባራዊ ስታደርግ የቆየች አገር ናት። እንደሚታወቀው የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ስራ በአንድ ጀንበር የሚከናወን ተግባር ሳይሆን በባህሪው ተከታታይነት ያለው ውይይት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ህብረተሰቡ በየደረጃው የሚያረገው አስተዋፅኦ ድምር ውጤት የሚያመጣው ለውጥ ነው። የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ተግባራት እንዲመጡ የሚያስገድዱ ምክንያቶች እጅግ በርካታ ቢሆኑም በእነዚህ ውስጥ በጣም ወሳኝ የሆኑት የፍትህ ተደራሽነት ማነስ፣ ብቃትና ጥራት ያለው ፍትህ መቀነስ፣ የህዝብ እና

የግለሰቦች የሰብዓዊ መብቶች በበቂ ሁኔታ አለመከበር፣ የዳኝነት ነፃነት ተገቢውን ቦታ አለማግኘት፣ ዳኞች ስራቸውን የሚያከናውኑበት የስነ ምግባር ሁኔታ ማነስ ተጠቃሽ ናቸው።

በኢትዮጵያም ውስጥ ለበርካታ ዓመታት የፍርድ ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም አስፈላጊነት ታምኖበት የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። እነዚህ የማሻሻያ ስራዎችን በተመለከተ ከታሪካዊ ዳራው በመነሳት በየትኛው ዘመን ምን ምን ስራዎች እንደተሰሩ በስልጠና ማንዋሉ ላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባሮች ከ2003ዓ.ም ጀምሮ አሁን እስካለንበት 2013 ዓ.ም ድረስ ምን እንደሚመስል ተብራርቷል። የነበሩ ውስንነቶችና ጠንካራ ጎኖችም ተዳሰዋል።

ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች የህዝብንና የመንግስትን አመኔታ ሊያተርፉ የሚችሉት ስራቸውን በነጻነት፣ ገለልተኛነት እና በተጠያቂነት መንፈስ ሲሰሩ ከመሆኑም በላይ ዳኞች ችሎት በሚያስችሉበት ጊዜ እና ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ እንዲሁም እንደ ዳኛ ከማህበረሰቡ የሚጠበቅባቸውን የስነ ምግባር መርሆዎች በመጠበቅም ጭምር በአግባቡ ተግብረው ሲገኙ ነው። ከእነዚህ መርሆች አንጻር የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ስራዎች ሲተገበሩ በተለይም ከፍርድ ቤቶች ጋር የተያያዙ የሰብዓዊ መብቶችን በማክበርና በማስከበር ረገድ ያሉበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በስልጠና ማንዋሉ ለማካተት ተሞክሯል።

የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባሮች በተገቢው ቢፈጸሙ እንኳ ህበረተሰቡ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እንዲያውቃቸው ካልተደረገ ህብረተሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ ለማሻሻል አይቻለውም። ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ መረጃ ልዉዉጥ ማድረግ የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን ይህንኑ በተመለከተ ከአስፈላጊነቱ ጀምሮ እንዴትና በምን መንገድ መረጃ ልዉዉጥ መደረግ እንዳለበት በማንዋሉ ላይ ለማብራራት ተሞክሯል። ፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች መረጃ ልዉዉጥ ተግባርን በተመለከተ ልንከተላቸዉ የሚገቡ ስትራቴጅዎች፣መንገዶችና ዘዴዎች ምን እንደሚመስሉ ለመግለጽ ተሞክሯል።

ማሻሻያ ስራዎቹ ለህዝብ እንዲታወቁ በማስቻል ፍርድ ቤቶች፣ መገናኛ ብዙሀን ፣የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና ምን መሆን እንደሚገባዉ ለመለየትና ለማብራራት ተሞክሯል።

የችሎት ዉሎ ዘገባን በተመለከተ የፍርድ ቤት ስራን ለህዝብ ከማሳወቅ አንጻር ያለዉ ጠቀሜታ፤ መገናኛ ብዙሀን ተሳትፎ፣ የተሻለ የችሎት ዉሎ ዘገባ ለመስራት ልንከተላቸዉ የሚገቡ የመፍሄ ሀሳቦች ተዳሰዋል።

# ማውጫ


መግቢያ ........ 3

ምዕራፍ አንድ፡........ 8

የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች በኢትዮጵያ ........ 8

1.1. ጠቅላላ እይታ ........ 8

1.2. የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት ከ2003 - 2010 ዓ.ም........ 12

1.3. የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ከ2010 ዓ.ም ወዲህ........ 14

ምዕራፍ ሁለት፡........ 19

የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችና ሰብዓዊ መብቶች ........ 19

2.1. የአካል ጉዳተኞች መብቶችና የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ..... 19
2.2. ስርዓተ ፆታ እና የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ..... 21
2.3. ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ..... 24
2.4. የዳኝነት ነፃነት ..... 26
2.5. የዳኞች የስነ ምግባር ሁኔታ ..... 29
ምዕራፍ ሶስት፡ ..... 33
የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን ለህዝብ የማሳወቅ ጠቀሜታዎች ..... 33
3.1. የመረጃ ልዉዉጥ አስፈላጊነት ..... 34
3.2. የፍ/ቤት አመኔታን ማስመለስ ..... 34
3.3. የፍ/ቤቶችን ጥቅም ማስከበር፤ ..... 36
ምዕራፍ አራት፤ ..... 38
የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራም ማስተዋወቅና የባለድርሻ አካላት ሚና ..... 38
4.1. የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና ..... 38
4.2. የመገናኛ ብዙሀን አሰተዋፅኦ ..... 40
4.3. የመረጃ ልውውጥና የፍርድ ቤቶች ሚና ..... 41
ምዕራፍ አምስት፤ ..... 43
የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች የመረጃ ልውውጥ ላይ የሚገጥሙ ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ ..... 43
5.1. በፍርድ ቤቶች የተጠናከረ የህዝብ ግንኙነት የስራ ክፍል አለመኖር ..... 43
5.2. የፍርድ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እዉቀት ማነስ ..... 44
5.3. በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ዘንድ የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤት ነጻነትን ይጋፋሉ የሚል አስተሳሰብ መኖር 45
5.4. ፍርድ ቤቶች፣የመገናኛ ብዙሀንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት የግንኙነት መድረክ አለመኖር... 46
5.5. የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ለመዘገብ ፍላጎት ማጣት ..... 47
5.6. በመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ጋዜጠኞች የህግ እዉቀት አለመኖር ..... 47
ምዕራፍ ስድስት ..... 50
የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚረዱ ስትራቴጂዎች፣ መንገዶች እና ዘዴዎች ..... 50
6.1. የመረጃ ልዉዉጥ ስትራቴጂዎች ..... 50
6.2. የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ የመረጃ ልውውጥ የመገናኛ ዘዴዎችና መንገዶች ..... 52
ምዕራፍ ሰባት፤ ..... 55
የችሎት ውሎ ዘገባ ..... 55

7.1. መልካም የችሎት ውሎ ዘገባ እንዲኖር ምን ይደረግ? ........ 57
መደምደሚያ እና መፍትሄ ሀሳቦች ........ 60
ዋቢ መጽሀፍት ........ 62

# ምዕራፍ አንድ፡
# የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች በኢትዮጵያ

## 1.1. ጠቅላላ እይታ

በዚህ የስልጠና ማንዋል ክፍል አገራችን ኢትዮጵያ በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባሮች ረገድ በንጉሳዊ ስርዓት ስትተዳደር ከነበረበት የዘመናዊ መንግስት ታሪክ ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ የታዩ አንኳር አንኳር የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን ለማየት የሚሞከር ሲሆን ሰልጣኞች ምዕራፉን ሲያጠቃልሉ፡-

- በየጊዜው በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የፍርድ ቤት አደረጃጀቶችን ይገነዘባሉ፡፡
- በአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የተደረጉ የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ያብራራሉ፡፡
- በደርግ ዘመን የፍርድ ቤቶች ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር ይተነትናሉ፡፡
- በኢህአዴግ የመጀመሪያዎቹ የስልጣን ዘመን በፍርድ ቤቶች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ያብራራሉ፡፡
- ከ2003 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የተደረጉ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራዊ ተፈጻሚነታቸው ምን እንደሚመስል ያውቃሉ፡፡
- ከ2010ዓ.ም ወዲህ በፍርድ ቤቶች ላይ እየተካሄደ ያለውን የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን ይገነዘባሉ፡፡

ኢትዮጵያ ቀደምት የሀገረ መንግስት ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን በየዘመኑ የነበሩት ንጉሶች የመንግስትን አስተዳደር ሲያከናውኑ እንደቆዩ የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ በየጊዜው የነበሩት ንጉሳዊ አገዛዞች የዳኝነት ስራን እንደማንኛውም የመንግስት ስራ በማየት እና በመደረብ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ መሰረት ባለው መልኩ ሲከውኑት ኖረዋል፡፡[1] የንጉሳዊ ስርዓቱ እስከወደቀበት አጼ ኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን ድረስ ንጉሱ ህግ የማውጣት፣ ህግ የማስፈፀም እና ህግን በመተርጎም በሚቀርቡለት ጉዳዮች ላይ ፍርድ የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህ ስልጣኑም የማይደፈርና ፍፁም ነው፡፡[2]

በጥንታዊት ኢትዮጵያ የፍርድ ቤቶች ስራ የሚከናወነው በንጉሱና በተዋረድ ባሉ ሹመኞች አማካኝነት ሲሆን ስራ ላይ የሚውሉት ህጎችም ሀይማኖታዊ እና በአንዳንድ ጉዳዮችም ባህላዊ አሠራሮች ናቸው፡፡

---

[1] አሰፋ ፍሰሀ፣ፌደራሊዝም እና ልዩነትን ማቻቻል በኢትዮጵያ፡የንጽጽር ጥናት(ኔዘርላንድስ፣ዎልፍ የህግ አሳታሚዎች፣1997ዓ.ም) ገጽ 390

[2] ሄነሪ ስኮለር፣የኢትዮጵያ የህገ መንግስትና የህግ እድገት፡ ኢትዮጵ ህገ መንግት እድገት ላይ የተሰራ ጥናት ቮሊዩም I ፣ 1997 ዓ.ም ገጽ 159

ህጉን በመተርጎም ረገድ የሀይማኖት ተቋማት ሚና ከፍተኛ ሲሆን እነዚህ የእምነት ተቋማትም የራሳቸውን ፍርድ ቤት እስከ ማቋቋም ደርሰዋል፡፡ የክርስትና እምነትን በሚከተሉ የአገሪቱ ህዝቦች በዋናነት በጥቅም ላይ የሚውለው ፍትሐ ነገስት ሲሆን ይህንን ህግ ተርጉመው ለፍርድ ስራ የሚያውሉት ሰዎች እንዲሁ በዘፈቀደ የሚመረጡ ሳይሆን በሀይማኖት ትምህርታቸው በተለይም በፍትሐ ነገስት ላይ የተለየ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፣ በአስተሳሰባቸውም ከአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የተሻለ የንቃት ደረጃ ላይ የደረሱ እንዲሁም በስነ ምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡

አገሪቱ በዚህ አኳኋን የፍርድ ስራን እያከናወነች ከቆየች በኋላ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ይህንኑ የፍርድ አሰራር ይዞ መቀጠል ያልቻለች በመሆኑ በተለይም እ.ኤ.አ. በ1942 አገሪቱ አዋጅ ቁጥር 02/1942ን በማወጅ የፍርድ ቤቶቹን ተቋማዊ አወቃቀር አሻሽላለች፡፡[3] በዚህም መሰረት ፍ/ቤቶች አጥቢያ ዳኛ፤ ምክትል ወረዳ ፍ/ቤት እና በጠቅላይ ግዛት ፍርድ ቤትነት እራሳቸውን በማደራጀት እና ሌሎች ክልላዊና አካባቢያዊ ፍ/ቤቶችንም እንዲቋቋሙ በማድረግ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይህም የፍ/ቤቶችን አደረጃጀት በተመለከተ የተደረገ ማሻሻያ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል፡፡

እ.ኤ.አ. በ1955 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ህገ መንግስት የዳኝነት ነጻነትን በተመለከተ አገራት ህግ የማጽደቅ ግዴታቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ዳኞች ችሎት በሚያስችሉበት እና ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ስራቸውን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት ማከናወን እንደሚገባቸው ተደንግጓል፡፡[4] ይህ ተግባርም በተለይ የዳኝነት ነጻነትን በህግ እውቅና በመስጠት ረገድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ስራ ላይ የታየ ጉልህ መሻሻል ተደርጎ ሊታይ የሚችል ሲሆን ተግባራዊ ተፈፃሚነቱን በተመለከተ ውስንነት መኖሩ አያጠያይቅም፡፡

ኢትዮጵያ የፍርድ ስራ እያካሄደች ከቆየች በኋላ በተለይም በ1950ዎቹ መጨረሻ እና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ስር ነቀል ሊባል በሚችል መልኩ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በዋናነት የሚታዩት የፍ/ቤቶችን አደረጃጀት የሚቀይሩና የሚያሻሽሉ የፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ህግ እና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ-ሥርዓት ወጥቶ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም ቀደም ሲል የነበረውን የፍ/ቤቶች አደረጃጀት እንዲለወጥ አስችሏል፡፡

---

[3] ሮበርት አለን ሴድለር፣የኢትዮጵያ የስነ ስርዓት ህግ፣ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አታሚ፣1968 ገጽ 8
[4] አንቀጽ 120 እና 121ን ይመልከቱ፡፡

ከፍርድ ቤቶች አደረጃጀት በተጨማሪ በኮድ መልክ ተዘጋጅተው በህግ አውጭው የታወጁት ስድስቱ የህግ ኮዶች [5] ፍርድ ቤቶች የፍርድ ስራን በተገቢው ለማከናወን የሚያስችል እና ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ ስርዓትና የመሰረታዊ መብቶች ድንጋጌዎች በማስቀመጥ ተከራካሪ ወገኖች የተፋጠነ ፍትህ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ፤ በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ፍርድና ውሳኔዎች በአግባቡ እንዲፈጸሙ የሚያስችሉ፤ ተከሳሾች ሊከበርላቸው የሚገቡ መብቶች ምን ምን እንደሆኑና በምን አኳኋን መተግበር እንዳለባቸው የሚያመላክቱ ህጎችን በማውጣት ረገድ ፍርድ ቤቶች በዛው አግባብ እንዲሰሩ ጅማሮ መታየቱ በርግጥም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ስራ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ማየት ይቻላል።

የፍርድ ስራን ለመስራት በህግ ትምህርት ቤት ተምሮ ማለፍና የህግ እውቀት መጨበጥ አስፈላጊ ስለመሆኑ በወቅቱ በነበረው ንጉሳዊ ስርዓት ታምኖበት በቀድሞው አጼ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት ቤት ከመከፈቱም በላይ ለሙያው የተመረጡ ሰዎች ወደ ውጭ አገር ተልከው የህግ ትምህርት እንዲከታተሉ ተደርጓል። ይህም የዳኞችን ቁጥር እና የሙያ ብቃት ከማጠናከር አንፃር ከፍተኛ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባር ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል። በዚህም አገሪቱ በሂደት በፍርድ ቤት የፍርድ ስራ የሚሠሩ የሕግ ትምህርት የተማሩ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዳኞችን ማፍራትና የዳኝነት ስራ ማካሄድ ጀምራለች። በእርግጥ በአገሪቱ ውስጥ ከነበሩት ፍርድ ቤቶች እና ችሎቶች እንዲሁም ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ አንፃር የህግ ምሩቃኑ ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም በየጊዜው እየሠፋና እያደገ ሄዷል።

ከዳኞች ሙያ መሻሻል እና ከህጎች መስተካከል በተጨማሪ በንጉሳዊ አስተዳደር ዘመን ፍ/ቤቶች የራሳቸው የሆነ፣ የታወቀና ለወቅቱ ህዝብ ይመጥናል ተብሎ የታመነባቸውን የፍርድ ቤቶች ህንፃዎች በመዲናዋ አዲስ አበባና በአንዳንድ የክፍለ ሀገር ከተሞች ላይ ተገንብተዋል። በዚህ ረገድ የነበረው መሻሻል ቀላል የማይባል ከመሆኑም በላይ እስከ አሁንም ድረስ አገልግሎት የሚሰጡ ፍርድ ቤቶች የተገነቡበት ወቅት በመሆኑ ላቅ ያለ መሻሻል ታይቶበታል።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ከህግ ማስተካከልና ማውጣት ጀምሮ የዳኞችን አቅም እስከ ማሳደግ እና ህንፃዎች እስከ መገንባት ድረስ በዘለቀው የማሻሻያ ተግባራት አበረታች ቢሆንም የፍርድ ቤቶችን

---

[5] የፍትሐብሄር ህግ፣ፍትሐብሄር ስነስርዓት ህግ፣የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት፣የንግድ ህግ፣ የማሪታይም ህግ።

ነጻነት፣ የዳኞችን ተጠያቂነት፣ የፍትህ ተደራሽነት፣ በአጠቃላይ ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ከነበረው እምነት አንጻር ሲመዘን የራሳቸው ዉስንነት ያለባቸው መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

**ጥያቄ**

- በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በርካታ የፍርድ ቤት ማሻሻዎች የተደረጉ ቢሆንም ፍርድ ቤቶች ዋና መርህ የሆነው የዳኝነት ነጻነት በህግ ጭምር አልተከበረም። እንዴት? አብራራ?። (6 ደቂቃ)

በደርግ የአገዛዝ ዘመን የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ያልፈረሰ እና በተግባርም ስራ ሲሰራ የቆዩ ቢሆንም በወቅቱ የተመሰረተው መንግስት የሶሻሊስት አስተሳሰብ የሚያንጸባርቅ ከመሆኑም ባሻገር አገሪቱ የምትመራውም በዚሁ ርዕዮታዊ አስተሳሰብ መሆኑን በይፋ አውጇል። ከፍርድ ቤቶች ነጻነት መሻሻል አንጻር ሲታይ በአገሪቱ ዉስጥ ተመሳሳይ የሆነ የሶሻሊስት ርዕዮተ አለም የሚከተሉ ተገዳዳሪ የሆኑ የፖለቲካ ሀይሎች በመፈጠራቸዉ፤ የወቅቱ መንግስትም ወታደራዊ መንግስት በመሆኑ እና በሌሎች ተደራራቢ ምክንያቶች የተነሳ አብዝሀኞቹ የወንጀል ጉዳዮች የሚዳኙትና ቅጣት የሚተላለፈው ከፍርድ ቤት ዉጭ ባሉ ወታደራዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች አማካኝነት ነዉ። ይህም ሁኔታ የፍርድ ቤት ነጻነትን የሚጋፋ መሆኑ አያጠያይቅም።

የኢህአዴግ መንግስት የስርዓት ለውጥ ያመጣ ከመሆኑም በላይ አገሪቱ ለተከተለችው የፌደራል ስርዓት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ህገ መንግስት ማጽደቁ ይታወቃል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስትም የፍርድ ቤቶችን ነጻነት እና ሌሎች ፍርድ ቤቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘ ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች በተግባር ላይ ቢያውሏቸው የህብረተሰቡን አመኔታ ለማግኘት እንዲችሉ የሚያደርጉ የሰብዓዊ መብቶችን የያዙ ድንጋጌዎችንም አስፍሮ ይገኛል።[6]

የፍትህ ዘርፉን ለዘመናት ጎትተው የያዙትን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ በ1998 ዓ.ም የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችን የያዘ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ይፋ በማድረግ [7] እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ከአቅም ግንባታ ሚኒስቴርና በኋላም የፍትህና የህግ ስርዓት ምርምር ተቋም ሲያስተባብሩት ቆይተዋል። የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሙ ተግባራዊ ሲደረግ በተለይም የህግ አስከባሪ አካላት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም እና የህግ ትምህርት ስልጠናና የምርምር ማጠናከሪያ ንዑስ ፕሮግራም ላይ በየደረጃው ጉልህ

[6] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስትም በምዕራፍ 3 ስር የተመለከቱትን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማየት ይቻላል።
[7] የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር፣የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም የጥናት መነሻ ሪፖርት፣ 1998ዓ.ም ገጽ 5

የሆኑ ለውጦች ስለመታየታቸው በተለያዩ ሪፖርቶች ላይ ተገልፆ ይገኛል። ነገር ግን የፍርድ ቤት የማሻሻያ ፕሮግራም ስራዎች በሚፈለገው ደረጃ ሊከናወኑ አልቻሉም።

ይህንንም ተከትሎ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሙን በጠቅላይ ፍርድ ቤት በኩል እንዲሆን በመንግስት በኩል ውሳኔ ተሰጥቶ ከ2003 እስከ 2010ዓ.ም ድረስ ሊቆይ የሚችል የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች ተቀርፀው ወደ ስራ ተገብቷል።

**የመወያያ ጥያቄ**

- በ1998 ወደስራ የገባው የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ያልቻለው በምን ምክንያትነው? አብራሩ? (8 ደቂቃ)

## 1.2. የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት ከ2003 - 2010 ዓ.ም

የህብረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ በዘላቂነት ለመመለስ እንዲቻል የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በውስጡ 7 ግቦችን እና 9 ውጤቶችን ያስቀመጠ ሲሆን የሚጠበቁትን ውጤቶች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ 16 ፕሮጀክቶችን ቀርጿል። [8] የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሙ ዓላማዎች፡-

1. የዳኝነት ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓቶችን በማጎልበት ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ በማድረግ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው አገልግሎቶችን ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤
2. በፍርድ ቤቶች ውስጥ የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ የሴቶችን ተሳትፎ በዳኝነት በታው ላይ ማሳደግና በፍርድ ሂደቱም ለሴቶች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
3. የፍርድ ባለመብቶች በፍርድ ባገኙት መብት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ ለፍርድ ስርዓቱ አጋዥ የሆኑ አስተዳደራዊ ፍትህ የሚሰጡ አካላትን በማጠናከር የህብረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ በመመለስ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲጫወቱ ማስቻል የሚሉት ስለመሆናቸው የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሙ ላይ ተገልጾ ይገኛሉ ።

ማሻሻያ ፕሮግራሙ ይዞ የተነሳውን ዓላማና ግብ ለማሳካትም 16 የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ቀርፃል። እነዚህም የሰው ሀይል ልማት ፕሮጀክት፣ የፍርድ ቤቶች ውጤታማነት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣የፍርድ

[8] የፌደራል የፍትህና የህግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት፣የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም በፌደራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት፣2011ዓ.ም. ገጽ 12

አፈጻጸም ሂደት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ ፍርዶችና ብይኖች በህገ መንግስቱ መሠረት መሰጠታቸውን የሚያረጋግጥ ፕሮጀክት፣ የዳኞች ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓትን ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፤ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ህብረተሰቡ ፍርድ ቤቶችን የሚመዝንበትን አሰራር መዘርጊያ ፕሮጀክት፣ የፍርድ ቤቶች ተደራሽነት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ አማራጭ የሙግት መፍቻ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ የህንፃና ሌሎች ፋሲሊቲዎች ማሟያ ፕሮጀክት፣ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች፣ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ ወታደራዊና አስተዳደራዊ ፍትህ የሚሰጡ አካላትን ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፤ ነፃ የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮጀክት፣ በፍርድ ቤቶች የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደጊያ ፕሮጀክት የፍርድ ቤቶች አሰራር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፤ ለረዥም ጊዜ የተጠራቀሙ ሰነዶችና መዝገቦችን እና መጠበቂያ ማስወገጃ ፕሮጀክት እንዲሁም የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ትግበራ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ናቸው።

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ የተከናወኑ በርካታ ስራዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም ከላይ በተገለፁት ፕሮጀክቶች አማካኝነት የተከናወኑ ስራዎች ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል። በእነዚህ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ፍ/ቤቶች እጅግ ብዙ የማሻሻያ ተግባራት የፈፀሙ ቢሆንም ፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት ክንውን በዋናነት በሚለኩበት ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን አመኔታ በማምጣት ረገድ ሲመዘኑ እጅግ ብዙ ውስንነቶች ነበሩባቸው።

በዚህም መከናወን ሲገባቸው እና ውጤት መገኘት ሲኖርበት ውጤት ያልተገኘባቸው የስራ ሁኔታዎች መኖር በምክንያትነት ይጠቀሳል። ለምሳሌ፡- የዳኞች ምልመላና መረጣ ተግባራዊ የሚደረግበት መመሪያ ቢዘጋጅም በተግባር ውጤታማ አልሆነም። ይህም ሊሆን የቻለው የዳኝነት ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓት እንዳይጠናከር በውስጥም ሆነ በውጭ አካላት ጣልቃ የመግባት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችና ዳኞች ራሳቸው በተለያዩ ተፅዕኖዎች ነፃነታቸውን ማስከበር ባለመቻላቸው የተነሳስለመሆኑ በየጊዜው ከተደረጉ ግምገማዎችና ከሚወጡ ሪፖርቶች መረዳት ይቻላል።

የዳኝነት አሰራር እና አገልግሎት አሰጣጥን ለህዝብ ግልፅ ለማድረግ የኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያዎችን ለመጠቀም የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ የሚፈለገው ውጤት አልመጣም፤ የዳኞች ስነ-ምግባር ደንብ እና የስነ-ምግባር ግድፈት አቤቱታን አቀራረብ ስርዓት በፍጥነት ተግባራዊ ባለመሆኑ ውጤት

አልታየም፤ የፍርድ ባለመብቶች በፍርድ አፈፃፀም አገልግሎት እርካታ ያገኛሉ ተብሎ ቢጠበቅም የህብረተሰቡ ቅሬታ አልተቋረጠም። [9]

ምንም እንኳ የህንፃውን ግንባታ የማካሄዱ ሂደት አመርቂነት ባለው ሁኔታ የተሠራ ቢሆንም፣ አካል ጉዳተኞችንና ሌሎች አቅመ-ደካማ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ምቹ ያለመሆን ችግር አለባቸው። እነዚህ እና ሌሎች ያልተተገበሩ የማሻሻያ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተደማምረው ፍ/ቤቶች ከህዝብ ሊያገኙ ይገባ የነበረውን አመኔታ በተገቢው እና በተሟላ ሁኔታ ሊያገኙ አልቻሉም፣ ይባስ ብሎም ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለው አመኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ እንዲሄድ አድርጎታል። የሙስና እና ቀልጣፋ እንዲሁም ተደራሽ የሆነ የፍርድ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ችግር የፍርድ ቤቶቹ ተግዳሮቶች ሆነው ቀጥለዋል።

ከ2003 ዓ.ም - 2010 ዓ.ም ድረስ ከላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ቀርጸው ለመተግበር እንቅስቃሴ ያደረጉ ቢሆንም፣ ባላከናወኗቸው ተግባራት እና በታየባቸው ውስንነት የተነሳ የፍርድ ቤቶች የህዝብ አመኔታ እያሽቆለቆለ የመጣባቸው ተቋማት ሆነዋል። ይህንኑ ተከትሎ አገራችን በ2010 ዓ.ም የመንግስት አመራር ለውጥ ማድረጓን ተከትሎ ፍርድ ቤቶችም አዳዲስ አመራሮችን ወደ መድረኩ እንዲመጡ አደርጓል።

**ጥያቄ**

- ከ2003 ዓ.ም - 2010ዓ.ም ድረስ የፍርድ ቤቶች የህዝብ አመኔታ እያሽቆለቆለ የመጣበትን ዋና ዋና ምክንያቶች ግለጽ? (6 ደቂቃ)
- የማሻሻያ ፕሮግራሙ ይዞ የተነሳውን ዓላማና ግብ ለማሳካትም ስንት ፕሮጀክቶችን ቀርጿል? በዝርዝር አስቀምጥ?

## 1.3. የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ከ2010 ዓ.ም ወዲህ

የዳኝነት ስርዓቱን ለማሻሻል እና የህዝብ አመኔታን ለመመለስ በማሰብ የዳኝነት ስርዓት ማሻሻያ አማካሪ ጉባዔ በማቋቋም ስራ ላይ ያሉትን አዋጆች በማሻሻል የዳኝነት አካሉን ተቋማዊ ነጻነትን እና ገለልተኝነትን የሚያረጋግጡ፤ የፍርድ ቤቶችን አስተዳደራዊ ስልጣን የሚያሰፉ፤ ውጤታማነትን ከቀድሞው የተሻለ

[9] ዝኒ ከማሁ የግርጌ ማስታወሻ 8 ገጽ 41-42

አደረጃጀት እና ስርዓት መዘርጋት የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች በማዘጋጀት እና በአዋጅ መልክ እንዲወጡ በማስቻል አመርቂ ውጤት አምጥቷል። [10]

የዳኞች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 684/2002ን የሚያሻሽለው አዲሱ አዋጅ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ስብጥር ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ የዳኞች ቁጥር በዘ እንዲል ተደርጎ የአባላቱ ቁጥር ወደ 15 ከፍ እንዲል ሆኗል። ጉባኤውም ራሱን በኮሚቴዎች በማደራጀት ተግባራቱን ማከናወን እንዲችል፣ ስልጣንና ተግባራቱም እንዲሰፉ ተደርጓል። ከዚህ በፊት የነበረውን እጥረት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የዕጩ ዳኞችን ምልመላ እና ሹመት ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር እና ግልጽ በሆነ መንገድ አስቀምጧል። በፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም ዝቅተኛ የዕድሜ ገደብንም ከ25 ዓመት ወደ 30 ዓመት ከፍ እንዲል አድርጓል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ከስራ ስለሚሰናበቱበት እና ለጥፋታቸውም ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ አካቷል፤ እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር ማሻሻያዎችን በማድረግ ተዘጋጅቷል።

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 እና ይህን አዋጅ ለማሻሻል የወጡ አዋጅ ቁጥር 138/1991፣ 254/1993፣ 321/1995 እና 454/1997 በመሻር አዲስ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ [11] እንዲዘጋጅና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ የተደረገ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ከነበሩት አዋጆች በተለየ ሁኔታ ያለንበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረጉ ስረ-ነገር ስልጣንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡ ሌሎች ከበፊቱ የተለዩና የተሻሻሉ ጉዳዮችንም እንዲይዝ ተደርጓል። የፌደራል ዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲስፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንብ ቁጥር 1/2013 ወጥቷል። ሌሎች ደንቦች እና መመሪዎች በመረቀቅና በመውጣት ሂደት ላይ ይገኛሉ። እነዚህ የህግ ማውጣት ተግባራት የፍርድ ቤቶችን ነጻነት፤ የዳኞችን ነጻነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የፍርድ ቤቶቹን የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ለማሳካት እንዲቻል እንደ ቅድመ ሁኔታ ከሚታየው ህጎችን የማሻሻል ተግባር አንጻር ሲመዘን ውጤታማ ስራ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

የማሻሻያ ስራዎቹ የሚታዩ ውጤትና ዘላቂነት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የ3 ዓመታት የማሻሻያ ፕሮግራም መሪ ዕቅድ በከፍተኛ ባለሞያዎች ተዘጋጅቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። በፕሮግራም ዕቅዱ ዝግጅት ወቅት ምክረ-ሃሳቦች ከዳኞች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞችና ከህግ ባለሞያዎች የተሰበሰበ ሲሆን፣ የልማት አጋሮች፣ ሲቪል ማህበራትና ባለሙያዎችም በረቂቁ ላይ በተለያየ ወቅት አስተያየት እንዲሰጡበት

---

[10] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዳኝነት አካሉ አሁናዊ ሁኔታና የወደፊት እይታ፣ታህሳስ 2012 ገጽ 1

[11] አዋጅ ቁጥር 1234/2013

ተደርጓል። በዚህ መልኩ የተዘጋጀው ዕቅድ 3 ዋና ዋና ግቦች ያሉት ሲሆን እነዚህም ግቦች የዳኝነትን ነፃነትና ተጠያቂነት ማጠናከር፣ የፍትህ ተደራሽነትን ማሳደግ እና የህግ ዕውቀትን ማዳበር፤ እና የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ የሚሉ ናቸው። እነዚህንም ግቦች ለማሳካት የሚረዱ 41 ፕሮግራሞች ተቀርጸዋል።[12]

በህገ-መንግስቱ አንቀጽ76(6) ፍርድ ቤቶች በጀታቸውን በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች አቅርበው እንደሚያስጸድቁ ይደነግጋል። ከዚህ አኳያ ለመጀመሪያ ጊዜ የ2012 ዓ.ም የበጀት ዓመት በራሳቸው በፍርድ ቤቶቹ እንዲዘጋጅ በማድረግ በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ተደርጓል። ይህ ተግባርም ተቋማዊ ነጻነትን ከማስጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ለውጥ የታየበት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን፣ ወደፊት አገሪቱ ከምትደርስበት የኢኮኖሚ ሁኔታ እና ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ ከሚያደርጉት አስተዋጾና ከሚያስገቡት ገቢ አንጻር እየታዬ በመጠን ደረጃ ሊሻሻል የሚገባው ነው።

የሰው ሀብት አቅርቦትን መጠን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ረዳት ዳኞችና ሬጅስትራሮች/የመዝገብ ቤት ባለሙያ ተሹመውና የሙያ ስልጠና ወሰደው ሥራ ጀምረዋል። ይህም አሁን ካለው የጉዳዮች ፍሰትና እና መዝገብ ጥራት ማነስ ጋር ሲተያይ በቂ ሊባል ባይችልም፣ መሻሻል የታየበት መስክ ነው ብሎ መወሰድ ግን ይቻላል።

ፍርድ ቤቶች ያለባቸውን የተቀላጠፈ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ለማሻሻል በማሰብ ይህንኑ ከሚያስፈጽሙና ከሚፈጽሙ ከውስጥ ሰራተኞች ጋር የመረጃ ልውውጥ ስራዎች ተሰርተዋል። የዳኝነት አገልግሎት ከሚጠይቁ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ድርጅቶች፣ በአጠቃላይ ከዜጎች ጋር የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ማከናወናቸውንና የመረጃ ልውውጥ ማድረጋቸውንም በግልጽ ማስተዋል ይቻላል።

የውስጥ ግንኙነት ስራዎች ፍርድ ቤቶች የህዝብ አመኔታን የመመለስ ዓላማ ላይ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር በየደረጃው ከሚገኙ ዳኞች፣ የልዩ ልዩ ስራ ክፍል ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ውይይቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ውይይቶች ፍርድ ቤቶች በሚሰጧቸው አገልግሎት ተገልጋይ እርካታ እንዳያገኝና አመኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሽቆለቁል ያደረጉ ምክንያቶች ነጥረው እንዲወጡ እድል የፈጠሩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ አመራሩ ወደፊት ሊሰራባቸው የሚገባቸውን የህዝብ ግንኙነት የመረጃ ልውውጥ ስራዎች በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በተለያዩ ህግ ነክ ጉዳዮችና ፍርድ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ የግንዛቤ መድረኮች

---

[12] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዳኝነት አካሉ አሁናዊ ሁኔታና የወደፊት እይታ፣ታህሳስ 2012 ገጽ 7

መካሄዳቸውን ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ስራ ሀላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅና ሰነዶች ማረጋገጥ ይቻላል።

የውጭ ግንኙነት ስራዎችን በተመለከተ በሀገር ውስጥ ባሉ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመራሮች እየተገኙ የተለያዩ ቃለ-መጠይቆች በማድረግ፣ ፍርድ ቤቱ ያደረጋቸውን ማሻሻዎያች በማስተዋወቅ አመርቂ ስራዎች ተሰርተዋል። በተያያዘም ፍርድ ቤቶች ያጡትን የህዝብ አመኔታ መመለስ እንዲያስችላቸው ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፤ የህግ ባለሙያዎች፤ ጠበቆች እና ሲቪል ማህበራት ጋር የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተዋል። [13] ተሳታፊዎችም በፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች በበቂ ደረጃ እንዲገነዘቡና ለችግሮቹ የመፍትሄ ሰጪ አካል በመሆን ሊያበረክቱት ስለሚችሉት አስተዋጽኦ ሃሳብ የተለዋወጡበት ውይይቶችም ተካሂደዋል።[14]

ከዚህ ጎን ለጎን በፍርድ ቤቶች እየተከናወኑ ያሉ ሁነቶችና ተግባራት እንዲሁም አፈጻጸም በጋዜጣዊ መግለጫ፤ በቃለ-መጠይቅ፤ በሪፖርት እና ጥቆማ በመስጠት መረጃን በማህበራዊ ሚዲያ እና በመደበኛው የብዙሃን መገናኛ (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ) መንገዶች በመጠቀም ለህብረተሰቡ የማድረስ ስራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ ባሻገር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያሉበትን አሁናዊ የለውጥ እንቅስቃሴና ነባራዊ ሁኔታ የሚያስገነዝቡ መረጃዎችን ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በመስጠት የፍርድ ቤቶችን መልካም ገጽታ የመገንባት ስራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

ጾታንና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ከመላከልና ምላሽ ከመስጠት አንጻር ነጻ ህግ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማስቻል ተሞክሯል። የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ተቋማዊ እንዲሆን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በተከናወነው ሥራ የሥርዓተ-ጾታን ጽንሰ ሐሳብ ማስረጽና በተቋሙ ውስጥም ጉዳዩ ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችልና የሚያግዝ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ገለጻ ከተደረገበት በኋላ ለሚመለከታቸው የተቋሙ አካላት ሁሉ ተሠራጭቷል።

ከላይ ከተገለጹት ከፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች አንጻር ሲታይ ፍርድ ቤቶች ከ2010 ዓ.ም ወዲህ መሻሻል የታባቸው ስራዎችን መስራታቸው መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም የፍርድ ቤት የማሻሻያ ተግባራት ውጤት ወዲውኑ የሚታይ ባለመሆኑ፤ ሌሎች ባለድርሻ አካትንና ህብረተሰቡን ተሳትፎ በእጅጉ የሚፈልግ

[13] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዳኝነት አካሉ አሁናዊ ሁኔታና የወደፊት እይታ፣ታህሳስ 2012 ገጽ 12
[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 12

በመሆኑና ይህንንም በአጭር ጊዜ ማሳካት የማይቻል በመሆኑ በተለይም የዳኞችን ነጻነት በማረጋገጥ ረገድ የሚጠበቁ ቀሪ ስራዎች በመኖራቸው፤ ተጠያቂነትን በተመለከተ ይህ ነው የሚባል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ባለመታየቱ፣ የዳኞች ብቃትና የስነ-ምግባር ሁኔታ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ባለመድረሱ፤ የፍርድ ቤቱ ሌሎች ሰራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ በሚታይ መልኩ ያልተሻሻለ በመሆኑ እና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በመኖራቸው የተነሳ በአገራችን ፍርድ ቤቶች የህዝብ አመኔታን በማግኘት ረገድ ውጤታማ ሆነዋል ለማለት አያስደፍርም።

## የመወያያነጥብ

- ከቀደመው ጊዜ በተሻለ ከ2010 ዓ.ም በኋላ የፍርድ ቤቶች የህዝብ አመኔታን ለመመለስ የተሰሩ ስራዎች ካሉ በዝርዝር ጥቀስ? ከ2003 ዓ.ም -2010 ዓ.ም ድረስ ካለው ጊዜ አንጻር ለውጥ አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ማሳያዎቹን በማነጻጸር ያስረዱ?

# ምዕራፍ ሁለት፡
# የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችና ሰብዓዊ መብቶች

ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የመንግስት አካል የመንግስት ስልጣናቸውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እንዳለባቸሁ ሁሉ እነዚሁ መብቶች በሌላ ሰው ተጥሰው ሲገኙ ያላቸውን ፍርድ የመስጠት ስልጣን በመጠቀም የማስከበር ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ እንደሚታወቀው መብቶች ሁሉ መነሻና ማጠንጠኛ የሰው ልጅ በመሆኑ ማንኛውም አይነት ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም በሚቀረጹበትም ይሁን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ የሰውን ልጅ ሰብዓዊ መብቶችን ታሳቢ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይህንን የስልጠና ክፍል ያጠናቀቀ ሰልጣኝ፡-

- አካል ጉዳተኞች በፍርድ ቤቶች ሊጠበቁላቸው የሚገቡ ልዩ መብቶችን ይገነዘባል፡፡
- የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች የአካል ጉዳተኞች መብቶችን ከማስጠበቅ አንጻር ያላቸውን ደረጃ ይገመግማል፡፡
- የስርዓተ ጾታን የሚመለከቱ መብቶች የትኞቹ እንደሆኑ ይለያል፡፡
- የዳኝነት ነጻነት ምን ማለት እንደሆነ ይገነዘባል፡፡
- የዳኝነት ነጻነት በአጠቃላይ የፍርድ ቤቶች ገጽታ ላይ የሚኖረዉን ውጤት ይተነትናል፡፡
- የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች ዉስጥ የዳኝነት ነጻነትን ያለዉን ቦታ ይገመግማል፡፡
- የዳኞች ስነ ምግባር በአጠቃላይ የፍትህ ሂደት ላይ የሚያመጣዉን ተጽዕኖ ያውቃል፡፡
- ስለ ፍትሀዊ የፍርድ ሂደት ግንዛቤ ይኖረዋል፡፡

## 2.1. የአካል ጉዳተኞች መብቶችና የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ

አካል ጉዳተኞች ተገቢውን የፍርድ ቤቶች አገልግሎት ለማግኘት የሚከለክላቸውን ምክንያቶች በዋናነት በሶስት በመክፈል ማየት የሚቻል ሲሆን እነሱም አንደኛ ህጎች፣ ፓሊሲዎችና አሠራሮች አካል ጉዳተኛውን ከተሳታፊነት ሲከለክሉ፤ ሁለተኛ አካል ጉዳተኞች ካላቸው ልዩ ፍላጎት አንፃር መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ተግባራት በበቂ ሁኔታ አለመኖር ለምሳሌ፡- የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አለመኖር፣ በፍ/ቤቶች ውስጥ የእያንዳንዱ የስራ ክፍል መገኛ ቦታ እና የሚያከናውነው የስራ አይነት አለመገለጹ፣ እንዲሁም በሶስተኛነት የሚታየው ከህንፃ ግንባታና ሌሎች ቢሮዎች አካላዊ ተደራሽነት እና አመቺነት ጋር በተያያዘ ለአካል

ጉዳተኛው አመቺ የሆነ የፍ/ቤቶች የህንፃ መግቢያ፣ የችሎት አሠራርና አቀማመጥ፣ የምስክር መቀመጫ፣ የመፀዳጃና ሌሎች አገልግሎቶች አለመሟላት በሚል ልናስቀምጣቸው እንችላለን፡፡

ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት የፍትህ ተደራሽነትን በተመለከተ አካል ጉዳተኞች እንደሌሎች ሠዎች ሁሉ የፍትህ ተደራሽነት መብታቸው ሊረጋገጥ እንደሚገባ ይህም የሚገልፀው በፍትህ አስተዳደር ውስጥ አካል ጉዳተኞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሲሆኑ እንደሆነ ደንግጎ ይገኛል፡፡ [15] በዚህ አለም አቀፍ ቃል ኪዳን ውስጥ የሰፈረውን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል አገራት ይህንኑ ቃል ኪዳን በአገር ውስጥ ህጎቻቸው ማካተት ወይም የህጎቻቸውን አተረጓጎም በተመለከተ ከዚሁ ቃል ኪዳን አንፃር እያስማሙ መተርጎሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

አንድ አገር ለአካል ጉዳተኞች የፍትህ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ህጎችን ፓሊሲዎችንና አሠራሮችን ሲያወጣ እና ሲተገበር የእነዚህኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምፅ መስማት የሚጠበቅ ሲሆን ህጎች ሲወጡም በተደራጁ ማህበራት በኩል ተሣታፊ እንደሆኑ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡ የሚወጡት ህጎች እና ፖሊሲዎች ከአለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ስምምነት/የቃል ኪዳን ሰነድ (CRPD) አንፃር ከተስተካከሉ በኋላ የአካል ጉዳተኞች የሰብዓዊ መብት ላይ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዳኞችና የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ ተከታታይና ወጥነት ያለው ስልጠና ማግኘት ይኖባቸዋል፡፡ ይህንንም ፕሮግራም ፍ/ቤቶች በመምራትና በማስፈፀም ረገድ ዋናውን የመሪነት ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ አገራችንም ይህንነኑ አለም አቀፍ ስምምነት ተቀብላለች፡፡

በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም በተለይም ከአካል ጉዳተኞች ልዩ ፍላጎትና የፍትህ ተደራሽነት አንፃር ሲታይ ከ2003 – 2010 ዓ.ም በተቀረፁት 16 የፍ/ቤቶች የማሻሻያ ፕሮጀክቶች ውስጥ በተለይም የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮቻቸውን ትግበራ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን በእነዚሁ ጊዜያት ውስጥ በጅምር ላይ ያለ ፕሮጀክት እንደሆነ እና ወደ መደበኛ ስራነት ያልተቀየረ ፕሮጀክት መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ከ2011 ዓ.ም በኋላም ቢሆን በሠው ሀይል ቅጥር እና ሌሎች አነስተኛ ለውጦች ከመታየቱ ውጭ ፍትህን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችሉ የተግባር ስራዎች ውጤታማነት አጠያያቂ ከመሆኑም

[15] አለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት አንቀጽ 13

በላይ ወደ መደበኛ ሥርዓትነትም ያልተቀየሩ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የ2012 ዓ.ም ሪፖርት ውስጥም በዚህ ረገድ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ በተብራራ ሁኔታ ተመልክቶ አይገኝም።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ባወጣቻቸው አዋጆችና ሌሎች ህጎች እንዲሁም ከተቀበቻቸው አለም አቀፍ የቃል-ኪዳን ሠነዶች እና ስምምነቶች አንፃር ሲታይ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተለይም በፍ/ቤቶች ሊኖር የሚገባው የፍትህ ተደራሽነት በህጎችና በፖሊሲዎች ረገድ ይህ ነው የሚባል የጎላ ችግር የሌለው ቢሆንም በተግባራዊ ተፈፃሚነታቸው ላይ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ እና ወደ መደበኛ ስራነት የተቀየረ ነው ሊባል አይችልም።

### የመወያያ ጥያቄዎች

- ፍርድ ቤት ማሻሻዎቹ የአካል ጉዳተኖችን ልዩ ፍላጎት ታሳቢ አድርገዉ ተቀርጸዋል ብለዉ ያምናሉ? መልሱ አዎ ከሆነ እንዴት? አይደለም ማሳያዎችን ይጥቀሱ።
- የኢትዮጵ ፍርድ ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ ናቸዉ መልሱ አዎ ከሆነ እንዴት? አይደለም ማሳያዎችን ይጥቀሱ።

## 2.2. ስርዓተ ፆታ እና የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ

የሴቶች የእኩልነት መብት የሰብዓዊ መብቶች አካል በመሆኑ የአንድ አገር የቤት ስራ ብቻ ተደርጎ የሚታይ አይደለም፤ በዚህም የተነሳ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ የዓለማቀፉን ማህበረሰብ ትኩረት አግኝቷል። በሴቶች ላይ የሚደርሰውን አድሎአዊ ልዩነቶች ለማስወገድ የሴቶች መብቶች በበርካታ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን። የተባበሩት መንግስታት ቻርተር ላይ ተመልክቶ እንደሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ዋና ዓላማ የሰብዓዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነፃነቶች በዘር፣ በቋንቋ፣ በፆታ ወዘተ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግባቸው ለሁሉም ተግባራት እንዲሆኑ ዓለም አቀፍ ትብብርን ማጠናከርና ማሳደግ አስፈላጊ ነው። ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫም ሰዎች ሁሉ እኩል ክብርና መብቶችን ይዘው መፈጠራቸውንና ነፃ መሆናቸውን ደንግጓል። በተጨማሪም በአንቀጽ 16 ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃ ፍቃድ ብቻ ላይ መመስረት እንደሚገባው እና ሴቶች በራሳቸው ነፃ ፈቃድ ጋብቻቸውን መመስረት እንደሚችሉ ተመልክቶ ይገኛል።

ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት ጾታን መሰረት ያደረገ አድሎን በመገንዘብ አባል መንግስታት በሰነዱ የተደነገጉትን መብቶች ያለ ምንም ልዩነት ለሴቶችም እንዲከበርላቸው ተገቢ የሆኑ

እርምጃዎችን እንዲወስዱ ሲያመለክት በአንቀጽ 2 ስርም ግዴታ ጥሎባቸዋል። በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 3 መሠረት አባል መንግስታት በሰነዱ ውስጥ የተካተቱትን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ወንዶችና ሴቶች እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፤ በተጨማሪም በስምምነቱ አንቀጽ 23 ጋብቻ የሚመሠረተው በተጋቢዎች ነፃ ምርጫ እና ፍላጎት ላይ ብቻ በመመስረት መሆኑንና ሴቶች ጋብቻው ሲመሠረት፣ ጋብቻው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜና ጋብቻው በሚፈርስበት ጊዜ ሁሉ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል።

ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት ልክ እንደ አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነቶች ሁሉ የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነት በአንቀጽ 3 ላይ የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ለአባል ሀገራት ሰጥቷል። ሴቶች ከወንዶች እኩል የስራ እድል የማግኘት፣ ለተመሳሳይ ስራ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ እንዲሁም አመቺ የስራ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው በአንቀጽ 7 ስር ተመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 10 ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች እኩል መብት ያላቸው መሆኑን እና የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብትን እንዳላቸው ደንግጎ ይገኛል። በሴቶች ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት በበኩሉ በሴቶች መብቶች እና የሚፈጠሩ አድሎአዊ ልዩነቶችን ለመከልከል የወጣ ስምምነት ሲሆን ባሉት 30 አንቀጾችም አድሎዓዊ ልዩነቶችን የሚከለክሉ፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን እና ጥበቃ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል።

በአገራችንም የሴቶች የእኩልነት መብቶችን ለማረጋገጥ እንዲያስችል በማሰብ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 35 በርካታ የሴቶችን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ዋስትና የሰጠ ሲሆን የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብትን ጨምሮ ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የመጠበቅ፣ በሀገሪቱ በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች የመሳተፍ መብት፣ የውርስ፣ የመሬት ባለቤትነት የማስተዳደርና የማስተላለፍ መብት፣ ስራ የመቀጠር መብት፣ የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህን መብቶች ለማስፈፀም የሚያችሉ በርካታ ህጎች ወጥተዋል፤ ሥርዓተ-ፆታን መሠረት ያደረገ ልዩነት የሚያስተናግዱ በስራ ላይ የነበሩ ህጎችንም የማሻሻል ተግባራት ተከናውነዋል። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከላይ ያየናቸውን አብዛኞቹን ስምምነቶች ተቀብላለች። በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁት ሁኔታዎች መረዳት የሚቻለው በፖሊሲና በህግ ማዕቀፍ ረገድ ኢትዮጵያ የሴቶችን የእኩልነት መብት ከማስጠበቅ አንፃር አበረታች ደረጃ ላይ ያለች መሆኗን ነው።

በመሠረቱ አገራችን በምታወጣቸው ህጎችና አጠቃላይ ፖሊሲዎች አንፃር የሴቶች የእኩልነት መብቶች መረጋገጣቸው ብቻውን በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶች መብቶች በተጨባጭ ተረጋግጠዋል ወደሚል መደምደሚያ ሊያደርስ አይችልም፡፡ ይልቁንስ ይህንኑ የሴቶችና የእኩልነት መብቶች ለማረጋገጥ እንዲቻል ሁሉም የመንግስት ተቋማት፣ ባለድርሻ አካላት እና ማህበረሰቡ በአጠቃለይ መጫወት የሚገባውን ሚና በመለየት ለተግባራዊ ተፈጻሚነታቸው መረባረብ ይገባዋል፡፡ ወደ ፍ/ቤቶችም ስንመጣ እንደ አንድ የመንግስት አካልነታቸው እነዚህ የሴቶች ሰብዓዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩ ሀላፊነት የሚኖርባቸው ሲሆን ወደ ስራ ለመቀየር ከላይ ከተመለከቱት አለም አቀፍና የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች ጋር ሊስማማ የሚችል የፍ/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ቀርጸው ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች በተመለከተ ከ2003 ዓ.ም - 2010 ዓ.ም የጊዜ ሠሌዳን የሚሸፍን የተለያዩ ፕሮግራሞች የተቀረፀ ሲሆን፣ የሴቶችን መብቶች በማረጋገጥ ረገድ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ትግበራ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ፕሮጀክት መቀረጹ ይታወቃል፡፡ ፕሮጀክቱም የፆታ-እኩልነትን ለማስከበር በፍ/ቤቶች የሚተገበሩ ፖሊሲዎች እና የአሠራር ስርዓቶች የሴቶችን እኩልነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በህገ-መንግሰቱ ለሴቶች የተረጋገጡ መብቶችን፣ የሴት ልጅ ጥቃት መንስዔዎችንና መፍትሄውን አስመልክቶ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ስልጠናዎችን ለፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ ለመስጠት መቻሉን ከፍርድ ቤቶቹ ዓመታዊ የስራ ሪፖርቶች ማወቅ ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመከታተያ የማረጋገጫ ዝርዝር/ቼክ ሊስቶች/ ተዘጋጅተው የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ [16]

የሴት አመራሮችን አቅም የሚያጎላብቱና ወደ አመራርነት ለማምጣት የሚያግዙ የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎችና የትምህርት እድሎች ተመቻችተዋል ፤ የፀረ ፆታ ጥቃት ቀንና የነጭ ሪቫን ቀን ፣ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንዲታወስና ሰራተኞች እንዲያከብሩት ተደርጓል፡፡[17] የሰው ሀይል መረጃን አሰባሰብም አደረጃጀትንም ስንመለከት ከስርዓተ ፆታ አኳያ ለመያዝ ተችሏል፡፡ [18]

---

16 የፌደራል የፍትህና የህግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት፣የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም በፌደራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት፣2011ዓ.ም. ገጽ 50

17 ዝኒ ከማሁ የግርጌ ማስታወሻ 16 ገጽ 50

18 ዝኒ ከማሁ ገጽ 50

ከ2010 ዓ.ም ወዲህም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በኩል በህገ-መንግስቱና በተለያዩ ህጎች መሠረት የተረጋገጡ የሴቶች መብቶች እንዲከበሩ የተለያዩ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎችን ለዳኞችና ለሌሎች ሠራተኞች እንዲሰጥ ተደርጓል፤ የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ ማንዋል በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የተቋሙ አካላት አሰራጭቷል፤ ሌሎችም ተግባራትን በመፈፀም ላይ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳን በፍርድ ቤቶች በኩል የሥርዓተ-ፆታ ጥቃት በተመለከተ የሚሠሩ ስራዎች መሻሻል የሚታይባቸው ቢሆንም አብዛኞቹ ዳኞች በፆታ ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለማስተናገድ አነስተኛ ልምድ ያላቸው በመሆኑ፤ የፍትህ መዘግየት በመታየቱ፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የውሳኔዎች መለያየት በመኖሩ የአንዳንድ ዳኞች የአመለካከት ችግር በመኖሩ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ከስርዓተ-ፆታ አንፃር ለውጥ ያለ ቢሆንም በበቂ ደረጃ ላይ አለመድረሱን መመልከት ይቻላል፡፡

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

- በኢትዮጵያ ውስጥ ስርዓተ ጾታ ጋር በተያያዘ የሴቶች ሰብዓዊ መብቶችን በተገቢው ሁኔታ እንዳይከበሩ የሚያደርጉ ተግዳሮቶች ካሉ ጥቀስ? የመፍትሄ ሀሳብም አቅርብ?
- ሴቶችን ጥቃት ከመከላከል አንጻር በአገራችን ተፈጻሚነት ያላቸዉ የህግ ማዕቀፎች የትኞቹ እንደሆኑ አብራራ?

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች በፍርድ ቤቶች በኩል እንዲከበሩ ለማስቻል በዋናነት ከዚህ በታች የተመለከቱት መርሆዎች ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባና በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞች ውስጥም ሊካተቱ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ከዚህ አኳያ እነዚህኑ መርሆዎች መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 2.3. ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት

በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ሰዎች በተፈጥሮ ያገኟቸውና በህግ የታወቁላቸዉ ሰብዓዊ መብቶች በህግ ከመዘርዘራቸዉ ባሻገር በተለይም በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥላቸዉ ለማስቻል ፍርድ ቤቶች የፍትሐዊ ፍርድ ሂደት መርህን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ፍትሐዊ የፍርድ ሂደትን ለማረጋገጥ ዋና መሰረት የሆነዉ መብት የእኩልነት መብት ሲሆን ይህ መብት በዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 14(1) ላይ ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል የመታየት መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ

የቃል ኪዳን ሰነድ አንቀጽ 26 ላይ ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፤በመካከላቸውም ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል በማለት ይደነግጋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. አንቀጽ 25 ላይም ከላይ ከተጠቀሰዉ የቃልኪዳን ሰነድ ጋር በሚስማማ እና አንድ አይነት በሆነ አገላለጽ ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣በብሔር፣ብሔረሰብ፣በቀለም፣በጾታ፣በቋንቋ፣በሀይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ።

አንድ ሰው በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ ሆኖ በሚቀርብበት ወቅት ወይም በፍትሀብሄር ጉዳዮችም ላይ ቢሆን ተከራካሪ ወገኖች ጉዳቻቸውን ይዘዉ ፍርድ ቤት ቢቀርቡበት ጊዜ በተያዘው ጉዳይ ላይ የሚካሄደው የችሎት ሂደት ግራ ቀኞችን እኩል በማየት በፍትሀብሄር ስነ ስርዓት ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች እንደሁም በሌሎች ህጎች መሰረት ሊጠበቅላቸው የሚገባው ሁሉም መብቶች እንዲከበሩላቸው መደረግ የሚገባው ሲሆን ችሎቱም መካሄድ የሚገባው በግልጽ ለህዝብ ክፍት በሆነ ሁኔታ ነው።

ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት መኖር አለበት ተብሎ የሚታሰበው በብዙ ምክንያቶች እና መዳረሻ ግቦች መሰረት በመሆኑ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። አንደኛዉ ምክንያት የሰዎች የሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለመከላከል የሚጠቅም መሆኑ ነው፤ በሁለተኛነት መጥቀስ የሚቻለዉ በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሄር ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ፍርድ ተገቢውን የፍርድ ሂደት በሚያልፍበት ወቅት በስህተት የጥፋተኛነት ፍርድ እንዳያጋጥም በዚህም ንጹህ ሰዎች የተሳሳተ ፍርድ ሰለባ እንደዳይሆኑ ከመከላከል አንጻር የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ ያለው በመሆኑ ነው። በሶስተኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ምክንያት ምንአልባትም ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የተነሳ ስህተት ተፈጽሞ ሰዎች ሰብዓዊ መብቶች ተጥሰው ቢገኙ ይህንኑ ጉዳት በተቻለ መጠን ለመካስ እንዲቻል ማስቻሉ ነው።

የዳኝነት ገለልተኛነት እና ነጻነት ጥያቄ ውስጥ መግባት፤ በተወሰኑ ከባድ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ብቻ ካልሆነ በቀር ለተከሳሽ በመንግስት የሚመደብ ተከላካይ ጠበቃ አለመኖር ፤ በአንድ አንድ ችሎቶች ላይ የሚስተዋል ተከራካሪዎችን ያለማክበር ሁኔታ መታየት፤ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በበቂ ሁኔታ

አለመኖር፤ እንዲሁም በችሎት አዳራሾች ያለማስቻል ሁኔታዎች መኖራቸው በአገራችን ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት በተሟላ ሁኔታ እንዳይረጋገጥ የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

## 2.4. የዳኝነት ነፃነት

በዘመናዊ የህግ አስተሳሰብ የዳኝነት ነፃነት ፅንሰ ሀሳብ የዳኝነት ነፃነት ባለቤቶች ዳኞች ብቻ ሳይሆኑ ፍርድ ቤቶችን እንደ ተቋም የሚያጠቃልል ነው፡[19] የዳኝነት ነጻነት ጽንሰ ሀሳብን ለዚህ ፅሁፍ አቀራረብ በሚያመች መልኩ ሲተረጎም ዳኞች በአንድ በያዙት ጉደይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ከተከራካሪ ወገኖች በኩል ከሚቀርብ ክርክር፣ ፍሬ ነገር፣ ማስረጃና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ በስተቀር ውሳኔ አሰጣጣቸውም ሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከማንኛውም መንግስት አካል፣ ባለስልጣንና ግለሰብ አላግባብ ጣልቃ ገብነት ተፅዕኖና ግፊት ነፃ መሆንን የሚጠይቅ ሲሆን እንደ ተቋም ፍ/ቤቶች ዳኞችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን የማስተዳደር ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን ትርጓሜ እንወስዳለን፡፡[20] ይህም የዳኞች ምልመላ፣ ሹመት፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ከስራ ማሰናበት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን የመወሰን ነፃነት መኖር ማለት ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የበጀት መጠን ግምት አዘጋጅተው ለሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ ማቅረብና በጀቱም ከፀደቀ በኋላ ከስራ አስፈፃሚው አካል ጣልቃ ገብነት ውጭ በጀቱን የማስተዳደር ነፃነትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡[21]

ነፃ የሆነ ፍርድ ቤት የህግ የበላይነት መሠረታዊ ገፅታና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በህገ-መንግስቱ ወይም በሌላ ህግ መደንገጋቸው ብቻ በራሱ ለመብቶች መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡[22] እነዚህ መብቶች እውን ይሆኑ ዘንድ ነፃ ፍርድ ቤት እና የዳኝነት ስራቸውን በነጻነት የሚሰሩ ዳኞች መኖር አለባቸው፡፡

ነፃነት የሌለው ፍርድ ቤት የሰዎችን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ለማረጋገጥ አይችልም፡፡ በዜጎችና በመንግስት እንዲሁም በሰዎች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ሳቢያ የሚነሱ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ክርክሮችን ገለልተኛና ነፃ ሆኖ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፍርድ ቤት በሌለበት የህግ የበላይነት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ የህግ የበላይነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እና መልካም

---

[19] የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል ገጽ 5
[20] ዝኒ ከማሁ ገጽ 11
[21] ዝኒ ከማሁ
[22] ዝኒ ከማሁ ገጽ 13

አስተዳደር እውን ሊሆኑ አይችሉም። [23] ሰላምና ዘለቄታዊነት ያለው ልማትም ዋስትና አይኖረውም። የዳኝነት ነፃነት ለኢንቨስትመንትና ለኢኮኖሚ እድገት መሠረት ነው። ህዝቡና ባለሀብቱ በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ላይ እምነት እንዲኖራቸው በአንድ አገር ውስጥ የዳኝነት ነፃነትን ማስፈንና ማረጋገጥ ወሳኝ ነው። ስለዚህ ስለዳኝነት ነጻነት አስፈላጊነት ላይ ምንም ክርክር የለም። [24]

ጥያቄው ያለው የዳኝነት ነጻነት ስፋትና ተግባራዊ አፈፃፀሙ ላይ ነው። የዳኝነት ነፃነትን የሚመለከቱ፤ የዳኝነት ነፃነት መስፈኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ መስፈርቶች፣ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የመፍትሄ መንገዶች እና አገራት ሊከተሏቸው የሚገቡ ስልቶችን የሚጠቁሙ ዝርዝር ድንጋጌዎች በአለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ሰነዶች ላይ ያሉ ሲሆን እነሱም በዋናነት፡- የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነፃነት መርሆዎች ረቂቅ፤ የአለም አቀፍ ጠበቆች ማህበር የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛዎች፣የሞንትሪያል ፍትህ ነፃነት ሁሉን አቀፍ መግለጫ፤የተባበሩት መንግስታት የፍ/ቤት ነፃነት መሠረታዊ መርሆች እንዲሁም የፍ/ቤቶች ነፃነትና ገለልተኛነት ሁሉ አቀፍ መግለጫ ረቂቅ ይገኙበታል። [25] እነዚህ አለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ሰነዶች በአገራችን ላይ በቀጥታ አስገዳጅነት የሌላቸው ቢሆንም ማንኛውም አገር የፍርድ ቤቶችን ነፃነት ለማስጠበቅ ካሰበ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ አመላካች ሀሳቦችን የያዙ ናቸው።[26]

የዳኝነት ነፃነትን ለማስፈን በመጀመሪያ መወሰድ የሚገባው እርምጃ ለዳኝነት ነፃነት የህግ ጥበቃ ማድረግ ነው። ብዙ ሀገራት ለዳኝነት ነፃነት መርህ ህገ-መንግስታዊ እውቅናና ጥበቃ አድርገዋል፡[27]፡ በዚሁ መሰረት የዳኞች የስራ ዘመን ዋስትና፣ ሹመት፣ ከስራ መሠናበት ደመወዝና ሌሎች ጉዳዮችን በህገ መንግስታቸው እንዲካተቱ አድርገዋል። ከዚህ አንፃር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት በአንቀጽ 78 ላይ ነፃ የዳኝነት አካል የተቋቋመ መሆኑን በግልጽ የደነገገ ሲሆን በአንቀጽ 79 ላይ ደግሞ የዳኝነት አካሉ ከማንኛውም የመንግስት አካል፣ ከማንኛውም ባለስልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው በማለት ይደነግጋል። ዳኞችም የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፤ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በማለት ተመልክቷል።[28]

---

[23] የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል ገጽ 13
[24] ዝኒ ከማሁ
[25] ዝኒ ከማሁ
[26] ዝኒ ከማሁ
[27] ዝኒ ከማሁ
[28] የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል ገጽ 28

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ላይ የዳኛ የጡረታ አወጣጥ ሁኔታን አስመልክቶ የደነገገ ሲሆን፣ በአንቀጽ 76(6) ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አካሉን የሚያስተዳድሩበትን በጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል በማለት ደንግጓል። ሌሎች የፍርድ ቤቱን ጉዳዮችና የዳኞችን ዝርዝር አስፈላጊ ተግባራትን እንዲያከናውን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ እንዲቋቋም አድርጓል። ይህም የሚያሳየው የዳኝነት ነፃነትን በህግ እውቅና በመስጠት ረገድ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት በሚገባ እውቅና መስጠቱን ነው።

በተግባር ያለውን ተፈፃሚነት በተመለከተ ህገ-መንግስቱ ፍርድ ቤቱ ራሱን ችሎ በጀት ማፅደቅና ማስተዳደር እንደሚገባው የደነገገ ቢሆንም እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በጀታቸውን በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች አቅርበው እና አጸድቀው አያውቁም ይህም በፍርድ ቤቶቹ ተቋማዊ ነፃነት ላይ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እንደ አለም አቀፍ የዳኝነት ነፃነት ዝቅተኛ መመዘኛ መሰረት ዳኞች ከመደበኛው የዝውውር ስርዓት በስተቀር ከፈቃዳቸው ውጭ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር የለባቸውም። [29]ይህም የሚሆነው አንድ ዳኛ በዚህ መንገድ ብወስን በዚህ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ እዛወር ይሆናል የሚል ፍራቻ በአእምሮው እንዲቀረፅና ወደ ሌላ ቦታ ላለመዛወር ሲል ከህግ ውጪ ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግ ነው።[30] የዳኞች ዝውውር በህግ በግልፅ በተቀመጠ ምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። የዳኞች እድገት ደግሞ ተጨባጭ በሆነ መመዘኛዎች በተለይ ችሎታ፣ ስብዕናና ልምድ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል። እድገት እንዴትና በምን መመዘኛ እንደሚሰጥ በህግ በግልፅ መቀመጥ እንዳለበት የዳኝነት ነፃነት መርህ ይጠይቃል።[31] ከዚህ አኳያ የአገራችንን ሁኔታ ስናይ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኞች ዝውውርን የመወሰን ስልጣን የዳኞች አስተዳደር ገባኤ ነው። ይሁን እንጂ ዝውውር በምን ምክንያት በምን ጊዜ ውስጥ መፈፀም እንዳበት የሚገልፅ ህግ  የለም። እድገትንም በተመለከተ ግልፅ ሆኖ በህግ የተቀመጠ መመዘኛ የለም።

---

[29] ዝኒ ከማሁ

[30] ዝኒ ከማሁ

[31] ዝኒ ከማሁ

ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች ማረጋገጥ የሚቻለው የዳኝነት ነፃነት ህገ-መንግስታዊ እውቅና ያገኘ ጉዳይ ነው ቢባልም በተሟላ ሁኔታ የዳኝነት ነፃነትን ለማረጋገጥ ገና ብዙ ስራዎችን አቅደን መስራት የሚጠበቅብን መሆኑን ነው፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

የዳኝነት ነጻነትን በተመለከተ ያለዉ ጉድለት በምን በምን ረገድ የሚታይ ነዉ? በዝርዝር ዉይይት ይደረግበት፡፡ (12 ደቂቃ)

### 2.5. የዳኞች የስነ ምግባር ሁኔታ

ዳኞች ስራቸውን በነፃነት ሊያከናውኑ ይገባል፤ ከህግ በቀር በሌላ በማናቸውም ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ተፅዕኖ ሊደርግባቸው አይገባም ማለት ዳኞች በስራቸው በሚፈፅሙት ከመልካም ስነ-ምግባር ያፈነገጠና በማህበረሰቡ ዘንድ የፍርድ ቤቶችን አመኔታን የሚቀንሱ ተግባራትን እንዲፅሙ ያስችላቸዋል ማለት አይደለም፤ ፈፅመው ሲገኙም ተጠያቂነት አይኖርባቸውም ለማለትም አይደለም፡፡[32]

የዳኝነት ስራ ባህሪ ገለልተኛነት አመዛዛኝነት ሐቀኝነት፣ ታታሪነት፣ ቅንነት እና የህዝብ አገልጋይነት ስሜትን የሚጠይቅ ነው፡፡[33] ይሁንና ከዚህ አስተሳሰብና መርህ ውጭ የህዝብ ተቋማት በሆኑት ፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ዳኞች የህዝብን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ተግባራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ፤ ህግ ሊጥሱ ይችላሉ፤ የራሳቸውን የግል ፍላጎቶችና የፖለቲካ አስተሳሰብ ሊያራምዱ፣ አድሎ ሊፈፅሙ ይችላሉ፤ ሙስና በውሳኔዎቻቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡ ስራቸውን በቅልጥፍና ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ ዳኞች በዳኝነት ስራቸው መልካም ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ከሌለ በስተቀር በተቃራኒው ወገንተኛና ሙሰኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[34]

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት ውስጥ ከተቀመጡት መሠረታዊ ህገ መንግስታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ተጠያቂነት ነው፡፡ በህገ መንግስቱ ውስጥ የተቀመጡት የዳኝነት ነፃነት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችም አብዛኞቹ ተጠያቂነትንም በውስጣቸው የያዙ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ተጠያቂነት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ልዩ ባህሪ ነው፡፡ የተጠያቂነት መርህም በሶስቱም የመንግስት አካላት ላይ ተፈፃሚነት ያለውና ሊተገብሩት የሚገባቸው መርህ ነው፡፡ ስራቸውን በመልካም ስነ ምግባር የማይሰሩ ፍርድ ቤቶችና ዳኞች

---

[32] የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል ገጽ34

[33] ዝኒ ከማሁ

[34] ዝኒ ከማሁ

መኖር የዴሞክራሲያዊ ስርዓት እና የመልካም አስተዳደር ጠንቅ ከመሆን ውጭ የሚፈይደው ነገር የለም፡፡[35]

ፍርድ ቤቶችና ዳኞች የያዙት ስልጣን የህዝብ ስልጣን ነው፡፡ ህዝቡ የሉዓላዊነት ስልጣኑን ተግባራዊ ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ በተወካዮች አማካኝነት ነው፡፡ የፍርድ ቤቶችና የዳኞች የህዝብ ተጠያቂነት የሚረጋገጠው በህግ አውጭው በኩል ነው፡፡[36] በኢትዮጵያ ውስጥ ዳኞች የሚሾሙት በፌዴራላዊ ስርዓቱ መሰረት በፌደራል መንግስት እና በክልል መንግስት ደረጃ ሲሆንበፌዴራል ደረጃ በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን በክልሎች ደግሞ በክልል ምክር ቤቶች ነው፡፡ ስለዚህ የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኞችን፣ የክልል ምክር ቤቶች ደግሞ የክልሎቻቸውን ዳኞቻቸውን ስነ-ምግባር ይቆጣጠራሉ፣ ይቅርታ የማያሰጥ የስነ-ምግባር ጥሰት ተፈፅሞ ሲገኝም የዳኞችን ሹመት ይሽራሉ፡፡ [37]እነዚህ የህዝብ እንደራሴ ምክር ቤቶች የፍርድ ቤቶቹን በበጀት አጠቃቀም እና የፍርድ ቤቶችን ስራ እንቅስቃሴ በሚቀርቡሏቸው ሪፖርቶች ላይ በመንተራስ ተቋማቱን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ፡፡[38]

ዳኞች እንደማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ እና የመንግስት ተሿሚ የወንጀል ህጉን ተላልፈው ከተገኙ በወንጀል ይከሰሳሉ፤ ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙም ቅጣት ይጣልባቸዋል፡፡ ዳኞች ስልጣናቸውን አለአግባብ መጠቀም የለባቸውም፤ ዳኞች የህዝብ አገልጋዮች እንጂ ተገልጋዮች አይደሉም፡፡[39] የዳኝነት ስልጣንን ህዝቡን ለማገልገል መጠቀም አለባቸው እንጂ ለግል ፍላጎትና ጥቅም ማራመጃ መጠቀም የሌለባቸው መሆኑን ለአፍታ እንኳን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ [40]ይሄን በመዘንጋት ፍትህን በጥቅማ ጥቅም በመሸጥና በመለወጥ የዳኝነት ስራ ክብርን የሚያዋርዱ ዳኞች ከስራ መሠናበት ብቻ ሳይሆን በህጉ አግባብ በወንጀል ሊጠየቁ ይገባል፡፡[41] ከዚህ በመለስ ያሉ ጥፋቶችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች ባሏቸው አሠራሮች መሠረት ሌሎች የዲሲፒሊን እርምጃዎችን በመውሰድ የዳኝነት የስነ-ምግባር ተጠያቂነት መርህን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

---

[35] የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል ገጽ 39
[36]ዝኒ ከማሁ
[37]ዝኒ ከማሁ
[38] ዝኒ ከማሁ
[39] ዝኒ ከማሁ
[40] ዝኒ ከማሁ
[41] ዝኒ ከማሁ

**የመወያያ ጥያቄ**

- የትኛው የዳኞች የስነ-ምግባር ችግር ነው በይበልጥ ህዝብ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ የሚያሳጣው? ለምን? (10 ደቂቃ)

ዳኞች በችሎት አመራርና በውሳኔ አሰጣጥ የተከራካሪ ወገኖችን ሰብዓዊ መብቶችን በማክበርና በማስከበር ረገድ ተገቢውንና የሚጠበቅባቸውን ስራ የመስራት ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ገለልተኛ፣ ግልፅነት ያለው፣ ሚዛናዊና ቀልጣፋ ፍትሕ ለመስጠት ያስችላቸው ዘንድም ሊከተሏቸው የሚገቡ መልካም የችሎት እና የዳኝነት ስነ-ምግባሮች ሊኖሩ እንደሚገባ አጠያያቂ አይሆንም፡፡

በዚህ ረገድ ዳኞች ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር መርሆች ምን ምን እንደሆኑ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዳኞች ተነፃፃሪ ግዴታዎችም ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር የሚገልፅ ደንብ ሊዘጋጅ የሚገባው ሲሆን፣ ዳኞችም ይህንኑ የስነ-ምግባር መርሆችን እና ተነፃፃሪ ግዴታዎቻቸውን የያዘውን ሰነድ እንዲያገኙት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚያ በተጨማሪም በዚሁ የዳኞች የስነ-ምግባር ደንብ ላይ ስልጠናዎች ተዘጋጅተው የግንዛቤ ማስጨባጫ ስራዎች መሠራት ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ ያልተናነሣውና ምን አልባትም ዋነኛው ነገር ዳኞች በሚወጣው የስነ-ምግባር ደንብ አወጣጥ ሂደት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በዚህ አኳኋን ዳኞች የሚያውቁት የተገነዘቡትና የተሳተፉበት የስነ-ምግባር ደንብ ከወጣ በኋላ በየችሎቶቹ ተግባራዊ መደረግ የሚገባው ሲሆን በአግባቡ ከተተገበረም ፍርድ ቤቶች ከህዝብ ያጡትን አመኔታ የመመለስ ሀይል ይኖረዋል፡፡

ዳኞች በስራ ላይ ያለውን የስነ-ምግባር ደንብና ለመልካም የችሎት አመራርና የውሳኔ አሰጣጥ የማይመቹ ጥፋትን ፈፅመው በተገኙ ጊዜ የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦባቸው፤ የቀረበባቸውንም ክስ ለማስተባበል በቂ እድል ተሰጥቷቸው ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ በስነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንቡ መሠረት ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ውስጥ በተቀመጡት መሠረታዊ ህገ-መንግስታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ተጠያቂነት ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ ከተዘረጉት ስርዓቶች ውስጥ የዲስፒሊን ስርዓት አንዱ ነው፡፡ ይህም ለመሆኑ የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 79(4) እና 81(6) ድንጋጌዎችን ማየቱ በቂ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ የዳኝነት ነፃነት መርህ ጋር በተጣጣመ መልኩ በዳኞች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

አዲስ የወጣው የፌዴራል ዳኞች የስነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንብ ቁጥር 1/2013ዓ.ም የስነ-ምግባር መርሆችንና የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በዝርዝር አካቶ ይዟል፡፡ ደንቡ ሐቀኝነት፣ ታማኝነት፣ ግልፅነት፣ ቅንነት፣ የህዝብ አገልጋይነት፣ ገለልተኝነት፣ ህግን ማክበር እና ሌሎች ዝርዝር የስነ-ምግባር መርሆችን ያስቀመጠ ሲሆን ዳኞች ማድረግ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን የስነ-ምግባር መርሆች ዝርዝር ይፋ አድርጓል፡፡ እነዚህ መርሆች በሁሉም ዳኞች ሊከበሩና ሊተገበሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች የአጠቃላይ ማህበረሰቡንና የመንግስትን እምነት ሊያተርፉ የሚችሉት ዳኞች ችሎት በሚያስችሉበት ጊዜ እና ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ እንዲሁም እንደ መልካም ዳኛ ከማህበረሰቡ የሚጠበቅባቸውን አርዓያነት ያለው የስነ-ምግባር መርሆዎች በመጠበቅም ጭምር በአግባቡ ተግብረው ሲገኙ ነው፡፡

ይህ በማይሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው የውስጥ አሰራር በመከተል የዲሲፒሊን እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፡፡ ከዛም የዘለለ ጥፋት ሲገኝ ዳኛው ከስራው እንዲሰናበትና የወንጀል ተጠያቂነት እንዲመጣበት ማስቻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ማህበረሰቡ በፍርድ ቤቶች ላይ እምነት የማጣት ደረጃው ከፍ ይልና የመፍረስ አደጋ ይገጥማቸዋል፡፡ የሙስና መስፋፋትና ከቁጥጥር ውጭ መውጣትም ፍርድ ቤቶችን እንዲፈርሱ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

ከዚህ አኳያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስቱ ላይ ስለተጠያቂነት በተመለከተዉ ክፍል የዲስፕሊን ጉዳይ በዳኞች አስተዳደር እንዲታይ መደንገጉ፤ ፍርድ ቤቶችም የስነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንብ[42] ማውጣታቸው ሲታይ በህግ ማዕቀፍ ረገድ የጎላ ችግር አለ ለማለት የማያስደፍር ቢሆንም በፍርድ ቤቶች ከሚታዩ የስነ-ምግባር ጉድለቶች አንጻር በዚሁ አግባብ ቅጣት የተላለፈባቸው ዳኞች ቁጥር አነስተኛ እና የአስተማሪነት ደረጃውም ዝቅተኛ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ከህብረተሰቡ ሊያገኙት የሚገባውን አመኔታ አሳክተዋል ለማለት አይቻልም፡፡

### የመወያያ ጥያቄ

- የዳኝነት ነጻነት የሚረጋገጠዉ ዳኞች ስራቸዉን በነጻነት ሲሰሩ ነዉ የሚለዉ አስተሳሰብ ገዥ መርህ ሆኖ እያለ ዳኞች ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በዝርዝር አብራሩ?

[42] የፌደራል ዳኞች የስነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክስ ስነ-ስርዓት ደንብ ቁጥር 1/2013ዓ.ም

## ምዕራፍ ሶስት፡
## የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን ለህዝብ የማሳወቅ ጠቀሜታዎች

ይህ የማሰልጠኛ ማንዋሉ ክፍል በዋናነት የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን ለህዝብ ማሳወቅ አስፈላጊነት መሆኑን ከመግለጽ ባሻገር፣ የመረጃ ልዉዉጥ ተግባሩ የሚያመጣ ቸዉን ጥቅሞች ያብራራል፡፡

ይህንን ስልጠና በአግባቡ የተከታተለ ሰልጣኝ፡-

- የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን ለህብረተሰቡማሳወቅ የሚገባ መሆኑን ይገነዘባል፡፡
- ፍርድ ቤቶች በመረጃ ልውውጥ ተግባራቸው ሲያካሂዱ የሚያገኙትን ጥቅም ይረዳል፡፡

አሁን ያለው የአለም ተጨባጭ ሁኔታ ባለ ብዙ ፈርጅ መገለጫ ያለው ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ አለም ወደ አንድ መንደርነት እየተቀየረች መጥታለች የሚለው አስተሳሰብ ገዥ ሀሳብ ሆኖ እየወጣ ይገኛል፡፡ በመሠረቱ ዓለም ወደ አንድ መንደርነት ተቀይራለች ሲባል በዋናነት የመረጃ ትብብርና ስርጭት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ በፍጥነት እየተላለፈ ይገኛል የሚለውን ሀሳብ የሚያካተት ነው፡፡ እንዲህ ባለው የተለወጠ የዓለም ሁኔታ ውስጥ መንግስት ባሉት የተለያዩ አካላቱ የሚሰራውን ስራ እና ያጋጠመውን ሁኔታ በተለይ ለባለድርሻ አካላት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ለጠቅላላው ህዝብ ለመግለፅና መረጃውን ለማዳረስ ይገደዳል፡፡ በዚህም የተነሳ የመገናኛ ብዙኃን እንደ አራተኛ የመንግስት አካል ሆነው የመቆጣር እሳቤ እውን እንዲሆን አስችሏል፡፡

አለም አሁን ባለችበት የመረጃ ልውውጥ ዘመን ተቋማት ስራቸውን ለህዝብ ሳያሳውቁ መልካም የሆነ ገፅታ ለመገንባት ይቻላቸዋል ብሎ ለማሰብ አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የዳኝነት አካሉም የተለየ አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የፌዴራል ስርዓት ውስጥ ሶስት የመንግስት አካላት ያሉ ሲሆን እነሱም ህግ አውጭ፣ ህግ አስፈፃሚና ህግ ተርጓሚ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሶስት የመንግስት አካላት ውስጥ በአንፃራዊነት የህግ አስፈፃሚውና የህግ አውጪው መንግስት አካላት በተሻለ ሁኔታ ለህዝብ ራሳቸውን

የሚያስተዋውቁ ሲሆን፣ የህግ ተርጓሚ የሆነው የዳኝነት አካል ግን ለብዙ ዓመታት በህዝቡ ዘንድ በደንብ የማይታወቅ እንዲሁም የተሳሳተ የህዝብ እይታ የሚያስተናግድ ሆኖ ቆይቷል። [43]

## 3.1. የመረጃ ልዉዉጥ አስፈላጊነት

ዓለም አሁን ባለችበት የመረጃ ልውውጥ ዘመን ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ለባለ ድርሻ አካላትና ለጠቅላላው ህዝብ የማስታወቅ የቀጥታ እና የተዘዋዋሪ ግዴታዎች የወደቁባቸው ሲሆን ከዚህ አንፃር ፍርድ ቤቶች የሚያደርጉትን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት ለባለድርሻ አካላትና ለህብረተሰቡ ማሳወቅ ይገባቸዋል። ይህን ሳያደርጉ እንደቀደመው ጊዜ ራሳቸው ዝግ ቢያደርጉ ከሚያተርፉት ይልቅ የሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች ይበዛሉ። ፍርድ ቤቶች የሚያወጧቸውን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለህብረተሰቡ በተገቢው ሁኔታ የመረጃ ልውውጥ ቢያደርጉ ህብረተሰቡ የሙብት ማስከበሪያ እና የግዴታዎች ማስፈጸሚያ ትክክለኛ ስፍራ አድርጎ ይወስዳቸዋል፤ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ፍርድ ቤቶች ፍትህ የመስጠት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ የሚል እምነት ይሳድራል፤ ይህም የፍርድ ቤቶችን ተቀባይነት ከፍ ያደርገዋል።

## 3.2. የፍ/ቤት አመኔታን ማስመለስ

ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ለረዥም ዓመታት የመንግስት የህግ አስፈፃሚው አካል ጣልቃ ገብነት፣ ለዳኝነት አገልግሎት አሠጣጥ እንቅፋት የሚሆኑ ህጎች መኖር፣ ከጉዳዮች ፍሰት መጨመር ጋር ተያይዞ ይህንኑ አገልግሎት በፍጥነትና በጥራት ለማከናውን የሚችል የዳኞች፣ የረዳት ዳኞች እና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ቁጥርና ክህሎቶች ማነስ እንዲሁም ሌሎች ችግሮች ተደማምረው ህብረተሰቡ በፍ/ቤቶች ላይ ያለውን አመኔታ እንዲቀንስ አድርገውት ቆይቷል። ይህንን የህዝብ አመኔታን መቀነስ ለማሻሻል በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞች ተቀርፀው የነበረ ሲሆን፣ ደረጃቸው የተለያየ ቢሆንም የማሻሻያ ተግባራትም ተፈፅመዋል፤ እየተፈፀሙም ይገኛል።

ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ቀርፀው ወደ ስራ መግባታቸው በአገሪቱ ህገ-መንግስት የተሰጣቸውን የህግ መተርጎም ስልጣን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፤ ህግንና ማስረጃን ብቻ መሰረት አድርገው ፍርድ እንዲሰጡ ይረዳቸዋል፤ ስራቸውንም በአግባቡ በነፃነትና በገለልተኛነት እንዲሰሩ

---

[43] ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ

ያስችላቸዋል፡፡ ይህም ለሀገር ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት የራሱን የማይናቅ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቶች ከላይ የተጠቀሱትን የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን መቅረፅና በቻሉት መጠን ተግባራዊ በማድረግ ብቻ ህዝቡ በፍርድ ቤቶች ላይ ያጣውን አመኔታ እንዲመልስ ያስችላል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንስ ህዝቡ በእርግጥም ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራትን በመፈፀም ላይ እንደሚገኙ መረጃ ሊደርሰው ይገባል፡፡ ለህብረተሰቡ የሚደርሰው የፍ/ቤቶች መረጃ የዳኝነት ነፃነትና ገለልተኛነትን ባልተጋፋ ሁኔታ የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ ከህዝብ አኗኗር እና ስነ-ልቦና ጋር የተጣጣመ በሆነ ጊዜ እንዲሁም የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ በተግባር ካለው የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ጋር የተስማማ ሲሆን ህብረሰተቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን የእምነት ማጣት በመተው ፍርድ ቤቶች ዜጎች እና በአገሪቱ የሚገኙ ሰዎች የመጨረሻ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ቦታ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኗቸው ማሻሻያዎች ለህብረሰተቡ በመረጃ ረገድ እንዲተዋወቁ ማድረግ ህዝብ በፍርድ ቤቶች ላይ ያጣውን እምነት ቀስ በቀስ ለመመለስ እንዲያስችል የሚረዳ አይነተኛ መሣሪያ ነው ብሎ ለመደምደም ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው አኳያ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችን በተለይም የፌዴራል ፍ/ቤቶች ያሉበትን ሁኔታ ስንገመግም ከ2003 ዓ.ም - 2010 ዓ.ም ድረስ የተቀረፀ በፍርድ ቤቶች የህብረሰብ ተሳትፎ ማሳደጊያ ፕሮጀክት የነበረ ሲሆን በዚህ ፕሮጀክት መሠረትም ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር በመተባበር የፍትህ ሳምንትን በማክበር የፍርድ ቤቱን ስራ ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፤ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የፍርድ ቤት ባለሙያዎች እየቀረቡ ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ በመስጠት የመረጃ ልውውጥ ተደርጓል፤ እንዲሁም ህብረሰተቡ በእጩ ተመልማይ ዳኞች ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ [44]

እነዚህ ስራዎች ወደ መደበኛ ስራነት ተለውጠው በመተግባር ላይ መሆናቸው አበረታች ቢሆንም፣ ህብረሰተቡ ተሳትፎ የሚያደርግባቸው መድረኮች ውስን በመሆናቸው አመርቂ ውጤት አላመጡም፡፡ [45] ከ2010 ዓ.ም በኋላ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ስራዎችን የመረጃ ልውውጥ ሂደትን ስንመለከት አዲስ የአመራር ለውጥ መደረጉን ተከትሎ ከፍርድ ቤት የውስጥ ማህበረሰብ ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች የተደረጉ

---

[44] የፌደራል የፍትህና የህግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት፣የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም በፌደራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት፣2011ዓ.ም. ገጽ 35

[45] ዝኒ ከማሁ ገጽ 35

ሲሆን፣ እነዚህን ውይይቶች ለህዝብ ለማሳወቅ ተሞክሯል። ከዚህ በተጨማሪ በፍርድ ቤቶች እየተከናወኑ ያሉ ሁነቶችና ተግባራት እንዲሁም አፈፃፀም በጋዜጣዊ መግለጫ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በሪፖርት፣ በማህበራዊ ሚዲያና በመደበኛው የብዙኃን መገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ የማድረስ ስራዎች ተከናውነዋል። ይህም ፍርድ ቤቶች ያጡትን የህዝብ አመኔታ ለመመለስ እንዲቻል ከማድረግ አንፃር አስተዋፅዖ የጎላ ነው።

በአጠቃላይ በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና የለውጥ ተግባራት የፍርድ ቤትን ልዩ ባህሪ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለህብረሰተቡ መረጃ መስጠትና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ መቻል ፍርድ ቤቶች ያጡትን የህዝብ አመኔታ ለመመለስ የሚያስችላቸው አንደኛው መንገድ ነው ብሎ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ይቻላል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና የለውጥ ተግባራትን ለህብረተሰቡ ማሳወቅ ውጤታማ የሚሆነው ምን ምን ሲሟላ ነው? በዝርዝር አስረዳ?
- የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና የለውጥ ተግባራትን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ በፍርድ ቤቶች ላይ የሚያመጠው ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ ካለ በዝርዝር አስረዳ?

## 3.3. የፍ/ቤቶችን ጥቅም ማስከበር፤

የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን በበቂ ሁኔታ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ለህዝብ ማሳወቅ ለፍርድ ቤቶች ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታ የሚኖራቸው ሲሆን ከጠቀሜታዎቹም ውስጥ በሌሎቹ የመንግስት አካላት አይን የተከበረና በስልጣን የተስተካከለ የፍርድ ቤት ተቋም ለመገንባት ያስችላል፤ የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ትብብር ድጋፍ በማገኘት ዳኞችና ሌሎች የፍርድ ቤት ሠራተኞች ያለባቸውን ምቹ የስራ ቦታ እጥረት፣ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አለመከበር፣ በተለይም በአስፈፃሚው አካል የሚኖር አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነትን ለማስወገድና ለመቋቋም እንዲቻል መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮችና ሌሎች ለፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ተግባራት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለማሟላት እንዲቻል ፍርድ ቤቶች ለህግ አውጭው አካል የሚያቀርቡትን የበጀት እና ሌሎች ጥያቄዎች በቀላሉ ለማጸደቅ ያግዘዋል።

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ተግባራት ለህዝብ ማስታወቅ የሚያስገኘው ሌላው ጥቅም የፍርድ ቤትን ነፃነት እና ገጽታ በዘላቂነትና ተቋማዊ መሰረት እንዲኖረው በሚያደርግ መልኩ ማስጠበቅ መቻል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የህግ አስፈፃሚው አካል የሆኑ ፖለቲከኞች እና  የስራ ኃላፊዎች የፍ/ቤቱን ነፃነት በሚጋፋ አኳኋን በአንድ ጉዳይ ላይ ወይም በአጠቃላይ የፍርድ ቤቱ ተቋማት ስራ ላይ አሉታዊ አስተያየት የመስጠት አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡[46]  የሚሰጡት አስተያየት እና ተገቢ ያልሆነ ገለፃ ለህዝብ ተደራሽ በሆኑ መገናኛብዙሀን እንዲቀርቡ በሆነ ጊዜ የፍርድ ቤቶችን የህዝብ አመኔታ የመሸርሸር ሀይል ይኖራቸዋል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ መልካም የመረጃ ልውውጥ እና ስራን ለህዝብ የማስታወቅ ባህል ያለው ፍርድ ቤት በአስፈፃሚ አካል ባለስልጣናት እና በሌሎች ፖለቲከኞች የተነገረው እና የተገለፀው መረጃ ከህግ፣ ከአሰራርና ከአመንክዬ አንፃር መሠረት የሌለው መሆኑን ለህዝቡ ግልፅ በማድረግ በፍርድ ቤቶች ላይ አንዣቦ የነበረውን የፍ/ቤት ነፃነትና መልካም ገጽታ የመጣስ ሁኔታን በእጅጉ የመቀየር አቅም ይኖረዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ እስከ 2010 ዓ.ም ያለው የፍርድ ቤቶች የመረጃ ልውውጥና ለህዝብ የማስታወቅ ስራ አነስተኛ በሚባል ደረጃ የሚገኝ ሲሆን፣ ከ2010 ዓ.ም በኋላ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ፖለቲከኞች የፍ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ያልተገባ አስተያየት ሲሰጡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በኩል ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰጥ የመረጃ ልውውጥ እና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ተግባር ሲከናወን ይታያል፡፡

በህገ-መንግስቱ እና በሌሎች ህጎች ላይ በተቀመጠው አግባብ እንደ ሶስተኛ መንግስት አካል መታየት ብቻ ሳይሆን፣ በተግባርም የሚገለጽ ቁመና እንዲኖራቸው ለማድረግ የህዝብ ግንኙነት ስራ መስራት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በቀጥታ የሚሳተፉባቸው የምክክርና የማስታወቅ ስራዎች መሰራት ተጀምሯል፡፡ እነዚህ መሻሻሎች የፍርድ ቤትን ነፃነት እና ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ ያላቸው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ሊበረታታ ይገባዋል፡፡

[46] ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ

## ምዕራፍ አራት፤

## የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራም ማስተዋወቅና የባለድርሻ አካላት ሚና

የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን የማስታወቅ ተግባር በተለይም በዚህ ዘመን አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም ከተባለ ይህንን የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ ፍርድ ቤቶች ለብቻቸው የሚወጡት ተግባር ባለመሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በዚሁ ተግባር ላይ ትኩረት በማድረግ ሊሰማሩ ይገባል። ከዚህ አንጻር ባለድርሻ አከላት ምን አይነት ሚና ይጫወታሉ የሚለውን ለማየት እንሞክራለን።

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል በንቃት ከተከታተሉ በኋላ ፡-

- የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን ለህብረተሰቡ በማስታወቅ ረገድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አስተዋጽኦ ለማወቅ ይረዳል።
- የመገናኛ ብዙሀን የሚኖራቸውን በጎ አስተዋጽኦ ይተነትናል፤ የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽዕኖም ይመረምራል።
- የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ተግባሮችን ለህዝብ እንዲደርሱ በማድረግ ረገድ መስራት የሚገባቸውን ስራዎች ይገነዘባሉ።

### 4.1. የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና

የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን የማስታወቅ ተግባር በፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲሰራ በማድረግ የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል ተብሎ አይታሰብም። የመረጃ ልውውጥና የህዝብ ግንኙነት ስራ የአንድ ወገን የግል ተግባር ብቻ ሳይሆን በባህሪው የብዙ ባለድርሻ አካላትን ርብርብ የሚፈልግ ሰፊና ውስብስብ ተግባር ነው።

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት ለባለድርሻ አካላት እና ለብዙሀኑ ማህበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ በመጀመሪያ የፍርድ ቤቶቹን ፕሮግራሞች ማስተዋወቅ ይገባል ወይስ አይገባም ከሚለው ጥያቄ ጀምሮ የህዝብ ግንኙነት እና የማስታወቅ ተግባሩ እንዲሰራ ተብሎ ከተወሰነ የፍርድ ቤቶችን ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት በመሠረታዊነትም የፍርድ ቤትን ነፃነትና ገለልተኛነት በአንድ በኩል የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆችን በሌላ በኩል በማስቀመጥ ሚዛኑን በጠበቀ ሁኔታ እንዲሠራ የተለያዩ ስትራቴጂዎችንና ዘዴዎችን መቀየስ ያስፈልጋል። እነዚህን ተግባራት ደግሞ ፍርድ ቤቶች ብቻቸውን

ከሚሠራቸው ይልቅ በፍርድ ቤቶቹ ባለቤትነትና መሪነት ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ተሣታፊ እንዲሆኑ በማድረግ ቢሠራ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራት ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት ከሚያስችላቸው ነገሮች ውስጥ የህዝብ ግንኙነት ስራ አንዱ ቢሆንም የዳኝነት አካሉ ስራ በአንድ ጀንበር የሚከናወን ተግባር ባለመሆኑ ከባለድርሻ አካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር ተከታታይ ውይይቶችና የህዝብ ግንኙነት መድረኮች ማድረግን ይጠይቃል፡፡ እንደሚታወቀው የሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ ዘርፎች እና በተለያዩ የአገልግሎ አሰጣጥ ራሳቸውን በማዋቀር የሚቋቋሙ ሲሆን ከእዚህ ውስጥ የአጠቃላይ ህብረተሰብን ንቃተ ህሊና ከፍ ለማድረግ በማስተማር ስራ ላይ የሚሰማሩ ይገኙበታል፡፡

ፍርድ ቤቶችም በተለይም በሰብዓዊ መብቶች፣ የህግ-የበላይነት፣ ዲሞክራሲና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ተሠማርተው ከሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በሚያደርጉ ግንኙነት የህዝብ ግንኙነትንና መረጃ የመለዋወጥን ተግባር የፍርድ ቤቶች ነፃነትን በጠበቀ መልኩ አብረው ሊሠሩ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚወክሉት የማህበረሰብ ክፍል በመኖሩ ለፍ/ቤቱ እንደ ባለድርሻ አካላት የሚታዩ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የፍርድ ቤቱን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት ለማህበረሰብ በማስተዋወቅ ረገድ በሚያደርጉት ተሳትፎ እንደ አጋር የሚታዩ ናቸው፡፡

የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ ጥናታዊ ፅሑፎችን በመስራት፣ ለህዝብ ግንኙነት ስራው የሚያስፈልገውን ሀብት በማሰባሰብ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የፍ/ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን ለህብረተሰቡ እንዲተዋወቅ ከማድረግ ባሻገር፣ ከሌሎች የመንግስት አካላት የሚመጣ ያልተገባ ጣልቃ ገብነትና ጫናን በመከላለከል ረገድ በተለይም የሙያ ማህበራት እና ስራቸው ከህግ ጋር የተያያዙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚያገኟቸውን የህዝብ ግንኙነት መድረኮች በመጠቀም የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ባላቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች ህብረሰተቡን በማሳተፍና ተገቢውን ጥናት በመስራት፤ የጥናታቸውንም ግኝት ለፍርድ ቤቶችና ለባለድርሻ አካላት በማቅረብ ሊወስዱ የሚገቡ እርምጃዎች በጊዜ እንዲወሰዱ ለማስቻል ያላቸው ጠቀሜታም እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ፍርድ ቤቶች በራሳቸው የህዝብ ግንኙነት ቢሮ በኩል የሚሠሯቸውን የመረጃ ልውውጥ ተግባራት በሀሳብም ሆነ ሀብት በማሰባሰብ ረገድ አጋዥ በመሆናቸው የፍርድ ቤቶችን

የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት በተመለከተ እንደ ውስጥ ባለድርሻ አካል ተደርገው ሊታሰቡ ይገባል። ከዚህ አንፃር በተለይም ከ2010 ዓ.ም በኋላ የአገራችን ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን ለህብረተሰቡ እንዲተዋወቅ ለማስቻል ከሲቪል ማህረሰብ ድርጅቶች ጋር በጋራ እየተሰሩ እንደሚገኝ የፍርድ ቤቶቹን የ2011 ዓ.ም፣ የ2012 ዓ.ም እና የ2013 ዓ.ም ዓመታዊ የክንውን ሪፖርቶች በማየት መገንዘብ የሚቻል ነው። ይህ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት በጎ ጅምር ነው።

## 4.2. የመገናኛ ብዙሀን አሰተዋፅኦ

በቀደመው ጊዜ ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን ለህብረተሰቡ በማጋለጥ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ዝግጅት የሌላቸው ሲሆን፣ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ህዝቡ ከፍርድ ቤቶች የሚያገኘውን አገልግሎት የመረጃ ልውውጥ ተደረገም አልተደረገም ብቸኛው አገልግሎት ሰጪዎች ፍርድ ቤቶች በመሆናቸው ምርጫ የለውም የሚል እምነት በመኖሩ፤ ዳኞችና ሌሎች ሰራተኞች በስራ ላይ ለመቆየት የግድ በህዝብ መመረጥ የማይኖርባቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም ፍርድ ቤቶችና ዳኞች የሚጠበቅባቸው ህጉን በእኩልነትና በፍትሀዊነት በመተርጎም ያለ ልዩነት ውሳኔ መስጠት እንጂ የሚያደርጉትን ማሻሻያ እና የሚሠሩትን ስራ ለህዝብ ማስተዋወቅ አይደለም የሚል ከፍተኛ እምነት መኖሩ ነው።[47] በዚህም የተነሳ ፍርድ ቤቶች ከሌሎች የመንግስት አካላት አንፃር ሲታይ ለመገናኛ ብዙሀን ራሳቸውን ዝግ አድርገው ቆይተዋል።

ይሁን እንጂ አሁን ባለው የዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የሚያደርጓቸውን ማሻሻያዎችና የሚሠጧቸውን ፍርዶች በህዝብ ዘንድ እምነት የሚጣልበት ሆኖ እንዲገኝ ለማስቻል የግድ የመገናኛ ብዙሀን ጋር መስራትና ከህዝባቸው ጋር ተገቢውን የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህም የተነሳ አሁን ላይ አሸንፎ የወጣው አስተሳሰብ መገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶች አጋር እንጂ ባላንጣዎች አይደሉም የሚል ነው።

መገናኛ ብዙሀን ፍርድ ቤቶች የሚያደርጓቸውን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት ለብዙሀኑ የህብረተሰብ ክፍል እንዲታወቅ ለማስቻል የመረጃ ልውውጥ ሚናቸውን የሚወጡ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የመገናኛ ብዙሀንን ጥቅም ለማግኘት ከጋዜጠኞች እና ከመገናኛ ብዙሀን ጋር የተሻለ እና በመርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።

---

[47] ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ

የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን ለህዝብ ከማስታዋወቅ ባለፈ በፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚታዩ ውስንነቶችንና የህዝብ አመኔታን የሚቀንሱ ተግባራትን የፍርድ ቤቶችን ነፃነት በማይጋፋ መልኩ የማጋለጥ ስራ በመስራት ለመልካም አስተዳደር እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የራሳቸውን የላቀ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 4.3. የመረጃ ልውውጥና የፍርድ ቤቶች ሚና

ፍርድ ቤቶች የሚያወጧቸውን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና የሚያከናውኗቸውን ተግባራትን በተመለከተ ከህዘብ ጋር የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ብቻ ሳይሆን የጉዳዩ ዋና ባለቤት በመሆናቸው የተነሳ የመሪነት ሚናውን ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቶች ስለተቋማቸው አሁናዊ ሁኔታና የወደፊት እቅድ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለህብረተሰቡ መረጃ ሊያደርሱ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቶች በተለይም የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን ለህብረተሱ መረጃ በመስጠት ራሳቸውን ማስተዋወቅ የሚገባቸው ሲሆን በተለይም በፍርድ ቤቶች የህንፃ እና ተያያዥ የመሠረተ ልማት ጉዳዮች፣ በሰው ሀይልና በበጀት፣ በመዝገብ ፍሰት እና አስተዳደር፣ በዳኞች አሿሿም፣ በፍርድ ቤቱ ነፃነት እና ገለልተኛነት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ለውጦችን ለህብረሰተቡ በሚገባ ማሳወቅና የመረጃ ልውውጥ የማድረግ ሃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ይህንኑ ግዴታቸውን በዘረጉት የተሻሻለ መዋቅር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በብቃት ለመውጣት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከጠቅላላ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ተግባራትና ፕሮግራሞች የመረጃ ልውውጥ በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለህብረተሰቡ በሚያደርሱት መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮችን እንዲያስተካክሉ፤ ከአዘጋገብ እና ተያያዥ ጉዳዮች አንፃር በሚፈጠር ስህተት የፍርድ ቤቶቹ ነፃነትና ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ተብሎ ሲታሰብ ፍርድ ቤቶች ባላቸው ከፍተኛ ሀላፊነት የተቋሙን ነፃነት ለማስጠበቅ ሲባል ለህብረሰቡ ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት የፍርድ ቤቶችን መልካም ገጽታ ማስጠበቅ ይችላሉ፡፡ በተነሳው ጉዳይ ላይ የማሻሻያ ተግባራትና ፕሮግራሞች ካሉም ለህብረተሰቡ ማስታወቅ ይችላሉ፡፡

የመገናኛ ብዙሀን ለህብረተሰቡ መረጃ የመስጠት ተልዕኳቸውን በሚወጡበት ጊዜ ከሚኖርባቸው ውስንነት የተነሳ በፍርድ ቤት ተከሳሽ ሆኖ የቀረበን ሰው ንፁህ ሆኖ የመገመት መብትን በሚጎዱበት ጊዜ፤ እንዲሁም ጉዳዩን በማየት ላይ ባሉ ዳኞች ላይ ከሌሎች የመንግስት አካላት ወይም ከሶስተኛ ወገኖች

ጤናማ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት በሚርስበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ከህብረሰቡ ጋር የመረጃ ልውውጥ በማድረግ የሚመጣውን ተፅዕኖ ለማስቆም ወይም ለመቀነስ ይችላሉ።

የመረጃ ልውውጥ ቀውስ በብዙ ምክንያቶች የሚፈጠር ሲሆን ከፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አንፃር በማህበራዊ ሚዲያ ያልተገባና የተሳሳተ ምስል በፍርድ ቤቶች ላይ እንዲሰርጽ የሚያደርጉ መረጃዎች በሚለቀቁበት ጊዜ ፤ ህዝብ በፍርድ ቤቶች ላይ ጥቃት ለመፈፀም በሚነሳሳበት ጊዜ ፤ ህብረተሰቡ በዳኞች ላይ ጉዳት የሚያመጣ ነገር ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን አዝማሚያ በሚያሳይበት ወቅት ፤ የተረጋገጡ እና የታወቁ የጉዳይ አያያዝ እና አመራር ስህተቶች በፍርድ ቤቶች አመራሮች ሲሰሩ፣ የፍርድ ቤቱን መልካም ስም የሚያጎድፍ ነገር በጋዜጠኞች ሲደረግ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው ።

እንዲህ ባለ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በመረጃ ልውውጥ ተቀባይነት ያላቸውን ስልቶች በመጠቀም ያጋጠማቸውን ወቅታዊ ሁኔታ እና የተወሰደውን የመፍትሔ ሀሳብ ለህብረተሰቡ በመግለፅ ህብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ እንዲኖረው፤ በህብረተሰቡ ዘንድ መደረግ ያለባቸወንና የሌለባቸውን ነገሮች እንዲያውቁ ለማስቻል ተገቢውን መረጃ በማድረስ የፍ/ቤቱን ተቋማዊ እና ግለሰባዊ ነፃነት ማስጠበቅ፣ የፍ/ቤቱን ተዓማኒነት መመለስ የሚያስችሉ የመረጃ ልውውጥ ተግባር በመስራት ረገድ ፍ/ቤቶች ዋናውንና ቀዳሚውን ሚና ይጫወታሉ። [48]

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

- በዚህ ርዕስ ስር ከተብራሩት ባለድርሻ አከላት ባሻገር የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞች በማገዝ ረገድ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ካሉ እነ ማን እንደሆኑ በዝርዝር ጥቀስ? ሚናቸዉንም በዝርዝር አስረዳ?

[48] ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ

# ምዕራፍ አምስት፤

# የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች የመረጃ ልውውጥ ላይ የሚገጥሙ ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ

ከህግ አስፈጻሚውና ከህግ አዉጭው አንጻር ሲታይ ፍርድ ቤቶች በየጊዜው የሚቀርጿቸውን የማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቁ ለማስቻል የሚሰሩት የመረጃ ልውውጥ ተግባር እጅግ አነስተኛ ነው። ለዚህ በምክንያትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ነገሮች ያሉ ሲሆን ሰልጣኞች ይህንን የስልጠና ማንዋል ክፍል ሲያጠቃልሉ፡-

- የፍርድ ቤቶች የመረጃ ልውውጥ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ ይገነዘባሉ።
- የፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት የስራ ክፍል አለመጠናከር እንዴት የመረጃ ልውውጥ ተግዳሮት እንደሚሆን ይተነትናሉ።
- የፍርድ ቤቶች ህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እውቀት ማነስ በመረጃ ልውውጥ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ይገነዘባሉ።
- በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ዘንድ የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤት ነጻነትን ይጋፋሉ የሚል አስተሳሰብ መኖር የመረጃ ልውውጥ ላይ ያለውን ያልተገባ ተጽዕኖ ያብራራሉ።
- ፍርድ ቤቶች፣የመገናኛ ብዙሀንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት የግንኙነት መድረክ መኖር የመረጃ ልውውጥ ስኬታማነት የሚኖረውን ፋይዳ ይገነዘባሉ።
- የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ለመዘገብ ለምን ፍላጎት እንደሚያጡ ይረዳሉ።
- በመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ጋዜጠኞች የህግ እዉቀት አለመኖር ለመረጃ ልውውጥ ተግዳሮት መሆኑን በሚገባ ያብራራሉ ።

## 5.1. በፍርድ ቤቶች የተጠናከረ የህዝብ ግንኙነት የስራ ክፍል አለመኖር

በኢትዮጵያ ውስጥ ፍርድ ቤቶች የሚደርጓቸዉን ማሻሻያዎችና ተግባራት በራሳቸዉ የህዝብ ግንኙነት አማካኝነት ለህብረተሰቡ በማድረስ ረገድ ያላቸዉ ተሞክሮ እና ልምድ እጅግ በጣም አነስተኛ ነዉ። ይህ ላለመሆኑ ብዙ ተደራራቢ ችግሮች እና ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ እጥረቶች መከካል አንዱ ጠንካራ የሆነ ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት አለመኖር ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ሁኔታ እንኳ ብንመለከት ለብዙ አመታት የህዝብ ግንኙነት የስራ ክፍል የራሱ ዳይሬክቶሬት ኖሮት ስራውን

በባለቤትነት ለመስራት የሚያስችለውን የሰው ሀይል በማሟላት ተገቢዉን ስራ ለመስራት አልቻለም። ስራው ሲሰራ የቆየውም በሌሎች የስራ ክፍሎች በተደራቢነት ነው። ከቅርብ አመታት ወዲህ በየፍርድ ቤቱ የህዝብ ግንኙነትን ስራ የሚሰሩ አነስተኛ የስራ ክፍሎች የተቋቋሙ ሲሆን በዋናነት ሲሰሩ የቆዩት የፍርድ ቤቶች መጽሄት ማዘጋጀትና ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ማዳረስ፤ የቀጠሮ መመዝገቢያ አጀንዳዎችን አሳትሞ ለዳኞች መስጠት የመሳሰሉ አነስተኛ ስራዎችን ነበር።[49]

በተለይም ከ2010ዓ.ም በኋላ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የህዝብ ግንኙት ዳይሬክቶሬት በፍርድ ቤቱ ድረ ገጽ፣ በቴሌግራም ቻናል፣ በፌስ ቡክ ገጽ እና በመገናኛ ብዙሀን በኩል መረጃዎችን በተሻለ ሁኔታ ለማሰራጨት እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቶች ያጋጠማቸውን የህዝብ አመኔታ ማሽቆልቆልን በሚመጥንና ለመመለስ በሚያስችል መልኩ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራትን የያዙ መረጃዎች በተገቢው መንገድ ተላልፈዋል ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል። በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተቋቋመው የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በስሩ በሚገኙ ከ10 በማይበልጡ ሰራተኞቹ አማካኝነት የመረጃ ልውውጥ ስራውን በተቀላጠፈና በብቃት ከመስራት አንጻር የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ይቻለዋል ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ነው።[50]

ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ሰራተኞችና የስራ ክፍሎች ጋር በመናበብ፣በመቀናጀትና የጋራ አሰራር ስርዓትን በመዘርጋት የፍርድ ቤቶቹን የማሻሻያ ተግባራት ለህዝብ በማሳወቅ ረገድ ዉስንነቶች መኖራቸው የተቋሟቱን የህዝብ ግንኙነት የጥንካሬ ደረጃ አጠያያቂ ያደርገዋል።

### 5.2. የፍርድ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እዉቀት ማነስ

የህዝብ ግንኙነት ስራ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚከወን ሳይሆን የራሱ የሆነ ሳይንስ ያለው መረጃን ለአጠቃላይ ህበረተሰብ ወይም ለተወሰ የማህበረሰብ ክፍል የሚደርስበትን መንገድ፣ ሁኔታና ስትራቴጅ ምን መምሰል እንዳለበት የሚተነተንበትና ተግባራዊ ተፈጻሚ የሚደረግበት ራሱን የቻለ የተለየ ዕዉቀት የሚፈልግ ተግባር ነው። ለዚያም ነው የህዝብ ግንኙነት ስራ መሰራት የሚገባው ትምህርት ዝግጅታቸዉ እና

[49] ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ህትመት ውጤቶችና ኦዲዮቪዥዋልቡድን መሪ ጋር ከተደረገ ዉይይት የተወሰደ
[50] ዝኒ ከማሁ

የተግባር ልምዳቸው ከዚሁ ተግባር ጋር ተያያዥ የሆነና ለቦታውም በሚመጥኑ ሰዎች ነው ተብሎ የሚታሰበው፡፡

ከዚህ በመነሳት የፍርድ ቤቶችን የህዝብ ግንኙነት ተግባር እንዴት መምራት እንደሚገባው በምንመረምርበት ወቅት ሁለት ነገሮች መሟላት እንደሚገባቸዉ ይገለጥልናል፡፡ አንደኛዉ ጉዳይ እንደማንኛውም ተቋማት የፍርድ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች በትምህርት ዝግጅታቸው በሙያው የሰለጠኑ መሆን ይገባቸዋል የሚለው ሲሆን ሁለተኛውና እኩል አስፈላጊ የሆነው ከልዩ ባህሪው አንጻር የህዝብ ግንኙነት ባለሙያው የህግ ዕዉቀት ሊኖረው ይገባል የሚለው ሀሳብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ህግ ጋር የተያያዘ የመረጃ ልውውጥ ጉዳይ ለህብረተሰቡ በሚተላለፍበት ወቅት በጥንቃቄና በህግ ዕውቀት ካልተመራ የሚያመጣው አሉታዊ ውጤት እንዲሁ በቀላሉ ሊስተካከል የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ አንጻር የፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እውቀት ሲኖራቸው ፍርድ ቤቶች የሚያደርጓቸውን ማሻሻያዎች እና የችሎት ውሎ ዘገባዎችን የፍርድ ቤቱን ነጻነት በጠበቀ መልኩ ለህብረተሰቡ ለማድረስ ይችላሉ፤ ከእነሱ እውቅና ውጪ በመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤት ተግባራት የፍርድ ቤቶችን ነጻነትና የተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን በጣሰ ሁኔታ ተዘግበው ሲገኙ የማስተካከያ ዘገባ ለመስራት ይቻላቸዋል፡፡ የፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እውቀት የሌላቸዉ ሲሆኑ ግን እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎችን ለማስተካከል በሀላፊነት የመወጣት አቅም የማይኖራቸው በመሆኑ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች የመረጃ ልውውጥ ላይ በተግዳሮትነት የሚታዩ ይሆናሉ፡፡

### 5.3. በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ዘንድ የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤት ነጻነትን ይጋፋሉ የሚል አስተሳሰብ መኖር

በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሌሎች አገራትም ጭምር ቁጥራቸዉ ቀላል በማይባል ፍርድ ቤቶችና ዳኞች መገናኛ ብዙሀንን እንደ አንድ የፍትህ አጋዥ ባለድርሻ አካል አድርጎ ከመቁጠር ይልቅ እንደ ባላንጣ የመቁጠር አስተሳሰብ አለ፡፡ መገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶችን ስራ በተዛባ ሁኔታ ለህብረተሰቡ በማድረስ ፍርድ ቤቶችን እና የዳኞችን ነጻነት የመጋፋት አዝማምያ ይታይባቸዋል፤ እንዲሁም በሚሰሩት የችሎት ውሎ ዘገባም ጉዳዩን ከሚገባው በላይ በማጮህና ለአንድ ተከራካሪ የሚወግን ዘገባ በመስራት በፍርድ

ሂደቱም ላይ ሆነ በፍርድ አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ የሚል አስተሳሰብ በበርካታ ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች ላይ ይታያል።

በርግጥ ብዙ ፍርድ ቤቶችና ዳኞች ከላይ የተገለጸውን አስተሳብ እንዲሁ የፈጠሩት ሳይሆን በተግባር በመገናኛ ብዙሀን በሚፈጸሙ ስህተቶች ላይ በመመርኮዝ የሚደርሱባቸው ድምዳሜዎች መሆናቸው አያጠራጥርም። ይህ ሲባል ግን ሁሉም ወይም አብዛሀኞቹ የመገናኛ ብዙሀን ከላይ የተጠቀሱትን ስህተቶች ይሰራሉ ማለት አይደለም፤ የሚሰሩ ስህተቶችም ሁል ጊዜ ሆን ተብለዉ የሚሰሩ ናቸው ብሎ መወሰድም አይቻልም። የሆነ ሆኖ በፍርድ ቤቶችና በዳኞች በኩል እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ መኖር የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ተግባራት በስፋት ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ከማድረግ አንጻር አስቻይ ሁኔታን አይፈጥርም።

## 5.4. ፍርድ ቤቶች፣የመገናኛ ብዙሀንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት የግንኙነት መድረክ አለመኖር

የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን የሚመለከት የመረጃ ልውውጥ በአንድ ወገን ብቻ የሚከናወን ሳይሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚፈልግ ተግባር ነው። ፍርድ ቤቶች እያከናወኑ ያሉትን የማሻሻያ ተግባራት መረጃ በመያዝና በመመዝገብ ረገድ የራሳቸው ሚና ያላቸው ሲሆን ይህንኑ የተሰበሰበ መረጃ ለህብረተሰቡ ለማድረስ የመገናኛ ብዙሀን ሚና እጅግ የላቀ ነው። ትኩረታቸውን በፍትህ፣የሰብዓዊ መብቶች እና ዲሞክራሲ ላይ አድርገው የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም በበኩላቸው መረጃው ለህብረተሰቡ በሚደርስበት ወቅት የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሯዊ ነጻነትና የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች በሚያከብር ሁኔታ እንዲከወን ከማስቻል አንጻር የራሳቸዉን ሚና ይጫወታሉ። ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ከተሰማሩበት መስክና ካላቸዉ እምቅ አቅም አንጻር የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት ለህዝብ እንዲደርስና እንዲታወቅ የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት ይወጣሉ።

ይሁን እንጂ እነዚህ ባለድርሻ አካላትና ፍርድ ቤቶች በቅንጅትና በመናበብ ስራቸውን ካልሰሩና ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት በሚፈለገዉ ጥራትና ደረጃ ለህብረተሰቡ አይደርሰም፤ እንዲውያም በተገላቢጦሽ ለህዝቡ የሚደርሱት መረጃዎች የመጣረስ ባህሪ የሚያሳዩና የመረጃ ቀዉስ የማጋጠም እድሉም ሰፊ ይሆናል።

አሁን ባለዉ የፍርድ ቤቶች ተጨባጭ ሁኔታ የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ተግባራት ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ለዉጥ የሚታይ ሲሆን የመረጃ ልዉዉጥ ተግባሩን ከዚህም በላይ ይበልጥ ለማጎልበት

ፍርድ ቤቶችና ባለድርሻ አካላት የሚገናኙበት እና ግንኙነቱም የሚገዛበት የራሱ የሆነ እቅድና ማዕቀፍ ያለዉ መድረክ አለ ለማለት አይቻልም።

## 5.5. የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ለመዘገብ ፍላጎት ማጣት

መገናኛ ብዙሀን የሚዘግቧቸውንና እና ለአጠቃላይ ህብረሰቡ የሚያደርሷቸውን ዘገባዎች ስንመለከት ብዙውን የአየር ሰዓትና የጋዜጣ ክፍል የሚይዙት የማህበረሰቡን ትኩረት ይስባሉ ተብለው የሚታሰቡ ፍሬ ሀቆች እና የመዝናኛ ጉዳዮች ናቸው። ይህን ካልን መገናኛ ብዙሀን ለምን ሆነ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ራሱን የቻለ የዳሰሳ ጥናት የሚፈልግ ከመሆኑም በላይ የዚህ ማንዋል ዋና ትኩረት ባለመሆኑ በዝርዝር መሄድ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ይሁን እንጂ ሰልጣኖች ይህንን ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በዚሁ ነጥብ ላይ የራሳቸዉን የዳሰሳ ጥናት በመስራት ለተጠቃሚ ይፋ ያደርጋሉ ተብሎ ይገመታል።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ ጠቅላላ የሆኑ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎች ብዙን ጊዜ የሚገለጹት ሰፋፊ በሆኑ ፕሮግራሞችና ከእቅድ አንጻር የተሰሩ ስራዎችና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን የሚተነትን ሪፖርት በማዘጋጀት ነው። ይህ አይነቱ አቀራረብ ብዙ የአየር ሰዓት እና የጋዜጣ ክፍል የሚወስድ በመሆኑ፤ ከዚህ በተጨማሪም እንዲህ አይነቱ አቀራረብ በአብዛሀኛው ማህበረሰብ ዘንድ መሰላቸትን የሚፈጥር በመሆኑ፤ እንዲሁም መገናኛ ብዙሀን የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ፕሮግራም ስርጭትን በመንተራስ ገቢ የሚያስገኙላቸዉን ማስታወቂያዎችና ሌሎች ፕሮግራሞችን በሚፈልጉት መጠን ለማስተላለፍ የማያስችላቸዉ በመሆኑ የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞች በማሰራጨትና ለህብረተሰቡ እንዲደርስ በማስቻል ረገድ ዝቅተኛ ፍላጎት ይስተዋልባቸዋል።

በአንጻሩ በኢትዮጵያ ውስጥ መገናኛ ብዙሀን በተለይም ታዋቂ ሰዎች እና የመንግስት ባለስልጣናት ተካፋይ የሆኑባቸውን የወንጀል እና የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ፍርድ ሂደትና የሚሰጡ ፍርድና ዉሳኔዎችን የሚመለከቱ የችሎት ውሎ ዘገባዎችን ለመስራት እና ለህዝብ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ፍላጎት የሚያሳዩ ሲሆን በዘገባው ያልተሳተፉትም የመገናኛ ብዙሀን ከሌሎች ምንጮች የሚያገኙትን ዘገባዎች ሲያስተላልፉ ይታያል።

## 5.6. በመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ጋዜጠኞች የህግ እዉቀት አለመኖር

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና የሚሰሩ ተግባራትን ለህዝብ በማስተዋወቅ ረገድ የመገናኛ ብዙሀን ሚና እጅግ ከፍተኛ ሲሆን ስራውም መሰራት የሚገባው በሙያው በሰለጠኑ፣ ንቁና በቂ ልምድ ባላቸዉ ጋዜጠኞች በሚሆንበት ጊዜ ውጤቱ አመርቂ እንደሚሆን አጠያያቂ አይደለም።

እንደሚታወቀው ፍርድ ቤቶች የሚተረጉሟቸው ህጎች፣የሚጠቀሟቸው የህግ ቃላቶች እና የሚከተሏቸው ጥብቅ የስነ ስርዓት ደንቦች የራሳቸዉ የሆነ የተለየ ባህሪ ያላቸዉ በመሆኑ መረጃን ለህዝብ በማድረስ ረገድም መገናኛ ብዙሀን እነዚህን ልዩ ባህርያት ታሳቢ ማድረግ ይገባቸዋል። አንድ ምንም አይነት የህግ ዕውቀት የሌለው ጋዜጠኛ የችሎት ውሎ ዘገባን ወይም ሌሎች ጠቅላላ የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን በሚሰራበት ወቅት ከፍርድ ቤቶቹ የሀሳብ ክፍል እና ከህጉ ዓላማ እና መንፈስ ውጭ የመዘገብ አጋጣሚዎቹ በብዛት የሚስተዋሉ በመሆኑ የፍርድ ቤቱ ገጽታ ላይ እና የተከራካሪዎች ወገኖች መብቶች ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል።

በአለም ላይ ታዋቂነትን ያተረፉ እንደ ሲ.ኤን.ኤን. እና ቢ.ቢ.ሲ ያሉ የመገናኛ ብዙሀን ፍርድ ቤቶችን ተግባራት የሚዘግቡት የህግ እውቀት ባላቸዉ ጋዝጠኞችና ተንታኞች አማካኝነት ሲሆን እነዚህ በህግ እውቀታቸዉ አንቱታን ያተረፉ ጋዜጠኞችና ተንታኞች የፍርድ ቤቶችን ነጻነትና የተከራካሪ ወገኖችን መሰረታዊ መብቶች በሚገባ የሚያውቁ ስለሆነ የሚያስተላፉት ዘገባዎች በአንድ በኩል እነዚህን መብቶችና መርሆች ባስጠበቀ መልኩ በሌላ በኩል የህብረተሰቡን መረጃ የማግኘት መብት በሚያሳካ አኳኋን እንደሚሆን ይጠበቃል።

የአገራችን የመገናኛ ብዙሀን ተቋማትና ጋዜጠኞች የፍርድ ቤቶች ጠቅላላ ማሻሻያዎችን እና የችሎት ውሎ ዘገባዎችን የሚሰሩት ለእዚሁ ተግባር በተመደቡ የህግ እውቀት ባላቸው ጋዜጠኞችና ተንታኞች አማካኝነት አይደለም ። ይህም ባለመሆኑ አብዛኞቹ ዘገባዎቻቸው ትክክለኛውን የፍርድ ቤቶች የስራ ሁኔታ እና ውሎ ከማንጸባረቅ ይልቅ ስሜት የተጫናቸውና ገለልተኛነት የማይታይባቸው አቀራረቦችን የሚያስተጋቡ ሆነው እናገኛቸዋለን። እንዲህ ያለው አካሄድ የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ተግባራት ለህዝብ በማድረስ ረገድ እንደ ተግዳሮት ሊታይ የሚችል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የፍርድ ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የህግ እውቀት መኖር ለምን ይጠቅማል? በዝርዝር አስረዱ?
2. የመገናኛ ብዙሀን የመረጃ ልውውጥ ስራ የፍርድ ቤቶችን ነጻነትና የተከራካሪ ወገኖችን መብቶች እንዴት ይጋፋል? መገለጫዎቹን በዝርዝር አሳዩ?
3. የመረጃ ልውውጥ ተግባራት የህግ እውቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ሲሰራ የሚገኘውን ጥቅም በዝርዝር አስረዱ?

# ምዕራፍ ስድስት

# የፍርድ ቤቶች ማሻሻያዎችን የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚረዱ ስትራቴጂዎች፣ መንገዶች እና ዘዴዎች

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን የሚመለከቱ የመረጃ ልውውጥ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን ዓላማውን ለማሳካት በሚያስችል ሁኔታ መረጃው ለህብረተሰቡ የሚደርስበትን መንገድና መልዕክቱ ለህዝቡ በትክክል እንዲደርስ የሚያስችሉ ዘዴዎች ምን አይነት እንደሆኑ በመለየት እና ስትራቴጅ በመቀየስ የሚተገበር ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ክፍል ያለውን ስልጠና በሚገባ የተከታተለ ሰልጣኝ፡-

- የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን የሚመለከቱ የመረጃ ልውውጥ ለህዝብ ለማድረስ የሚረዱ ስትራቴጅዎችን አንድ በአንድ ያውቃል፡፡
- የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን የመረጃ ልውውጥ ለህዝብ ለማድረስ የሚያግዙ ዘዴዎችንና መንገዶችን ይለያል፡፡

ፍርድ ቤቶች የሚቀርጿቸውን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለህብረተሰቡ በማስተዋወቅ ረገድ ትክክለኛውን ስትራቴጂ፣ ከአስተማማኝና ከተደራሽነት አንፃር አዋጭ የሆኑትን መንገዶች እንዲሁም መረጃውን የሚያስተላልፉበትን ዘዴ ሳይለዩ በግርድፉ የሚያከናውኗቸው የመረጃ ልውውጦች የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት እና ፕሮግራሞች በተገቢው በህብረተሰቡ ተዋውቀው የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አያስችላቸውም፡፡

ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ ለመመለስ፣ የመረጃ ልውውጥ ቀውስ ባጋጠመ ጊዜ ከዚሁ ቀውስ በፍጥነት ለመውጣት፣ የፍርድ ቤቶቹን ተቋማትና የዳኞች ግለሰባዊ ነፃነት ለማስጠበቅ እና ገለልተኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚሠሩት የመረጃ ልውውጥ ስራዎች በተጠና ስትራቴጂ በሚታወቁ መንገዶች እና አዋጭ በሆኑ ዘዴዎች አማካኝነት መተግበር አለባቸው፡፡

## 6.1. የመረጃ ልዉዉጥ ስትራቴጂዎች

1. የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች የሚመለከቱ መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ካስፈለገ መረጃ ልውውጡ በፍርድ ቤት በተያዘ የተለየ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቶቹ በቀረጿቸው ጠቅላላ ማሻሻያ ፕሮግራሞችና በሚተገብሯቸው ተግባራት ላይ ማተኮር ይገባዋል። ከዚህም መገንዘብ እንደሚቻለው በአንድ በፍርድ ቤት ክርክር በሚደረግበት ጉዳይ ላይ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የፍርድ ቤቶቹን አጠቃላይ የማሻሻያ ተግባራት የሚያሳይ ቢሆንም እንኳ ህብረተሰቡ ለፍርድ ቤቶች ያለውን አጠቃላይ እይታ በተሟላ ሁኔታ የማያሳይ በመሆኑ በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ዋና ዋና ተግባራትም ላይ ተገቢውን መረጃ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የማድረግ የመረጃ ልውውጥ ስትራቴጂ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ነው።
2. ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኗቸውን የማሻሻያ ተግባራት ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ በዋናነት ሰፊ ሽፋን ያላቸውን መገናኛ ብዙሀን መጠቀም የሚገባቸው ሲሆን ካላቸው በጀትና ጊዜ አንጻር እየገመገሙ ማግኘት የሚችሏቸውን አዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ጨምሮ ሁሉንም አይነት ህጋዊ የመገናኛ መንገዶችና ዘዴዎች መጠቀም ይገባቸዋል። ይህም ስትራቴጂ የሚጠቅመው ፍርድ ቤቶች ህብረተሰቡን መርጦ በሚጠቀመው የመገናኛ ዘዴ እንደየፍላጎቱ መረጃውን ለማግኘት እንዲያስችለው ነው።
3. ፍርድ ቤቶች የመረጃ ልውውጥ ሲያደርጉ ከመረጃው አይነት በመነሳት ተደራሽ መሆን ያለባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በትክክል መለየትና የመረጃ ልውውጥም ለእነዚሁ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲደርስ ማድረግ አስፈላጊ ነው።[51] ከዚህ አኳያ ትኩረት የተደረገበት የህብረተሰብ ክፍል መረጃ የሚቀበልበትን ሁኔታ መለየት ያስፈልጋል።
4. ፍርድ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ማሻሻያዎች በመነሳት ለህብረተሰቡ በጠቅላላው እንዲሁም ለባለድርሻ አካላት በተለየ ሁኔታ ሊደርስ የሚያስፈልገውን መረጃ በትክክል ማወቅና የመረጃውን መልዕክት መቅረፅ አስፈላጊ ሲሆን ይህም ፍርድ ቤቶች ከህብረተሰቡ ማግኘት ያለባቸውን መተማመንና እውቅና በተገቢው እንዲያገኙ ያግዛቸዋል። [52]
5. ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኗቸውን የመረጃ ልውውጦች ከጊዜና ከሁኔታ ጋር የተስማሙ እና ራሳቸውን ከወቅት ጋር እያሻሻሉና እያዘመዱ መሄዳቸውን መከታተልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባቸዋል።

---

[51] ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ
[52] ዝኒ ከማሁ

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- በስልጠና ማኑዋሉ ላይ ያልተጠቀሱ ሶስት የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራት መረጃዎች ለህዝብ ለማድረስ የሚረዱ ስትራቴጅዎችን ጥቀስ? (10 ደቂቃ)

## 6.2. የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ የመረጃ ልውውጥ የመገናኛ ዘዴዎችና መንገዶች

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና ተግባራት በአሁኑ ወቅት ለጠቅላላ ህብረተሰብ ለማዳረስ የሚረዱ ብዙ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች የተፈጠሩ ሲሆን ፍርድ ቤቶችም እነዚሁኑ የመገናኛ ዘዴዎችና መንገዶች በአግባቡ በመጠቀም በፍርድ ቤት እየተካሄደ ያሉትን የለውጥ ተግባራት እና በአንዳንድ የተለዩ ጉዳዮች ላይ በችሎቶች የሚኖራቸውን የፍርድ ሂደት ምን እንደሚመስል ለህዝብ ለማስተዋወቅ ይቻላቸዋል።

- **ጋዜጣዊ መግለጫ፡-** አዋጭ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ሲሆን ለብዙሀኑ በተመሳሳይ ሰዓት በመድረስ ረገድ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል። ጋዜጣዊ መግለጫ ለብዙሀን መገናኛ እኩል እድል ከመስጠት አንፃር፣ አንድ አይነት እና ወጥነት ያለው መረጃ ለህዝብ ከማድረስ አንፃር፣ የታለመለትና የተገደበ መረጃ ብቻ እንዲተላፍ ከማስቻል አንፃር፣ በተዛባ ሁኔታ መረጃ እንዳይተላፍ ከማስቻል አንፃር ሲታይ በእርግጥም አዋጭ የመገናኛ ዘዴ ወይም መንገድ ነው።
- **ጋዜጣዊ ጉባኤ**፡- ብዙ ጊዜ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች ያደረጉትን ማሻሻያ ጋዜጣዎች በአንድ ላይ በተሰበሰቡበት በፍርድ ቤት የስራ ኃላፊዎች ገለፃ ተደርጎ ከጋዜጠኞቹ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ተንተርሰው መልስ የሚሰጥበት መድረክ ወይም ጉባዔ ሲሆን መረጃን ለህዝብ ለማድረስ ጠቀሜታ እንዳለሁ ሁሉ በጥያቄና መልስ ሂደቱ ውስጥ በስራ ኃላፊዎች ያልታሰበ ሀሳብ እንዲወጣ የሚሆንበት አጋጣሚ እና ስጋት ይኖረዋል። ስለሆነም ይህንን መንገድ የሚጠቀም የፍርድ ቤት የስራ ሀላፊ በተቻለ መጠን ከተያዘው ርዕስ ባለመውጣት የጥያቄውን ምላሽ ቀደም ሲል የተሰጠውን ገለፃ ጋር በሚስማማ መልኩ የሀሳብ ፍሰትን በጠበቀ ሁኔታ መደረግ ይገባዋል።
- **ቃለ ምልልስ፡-** እንዲህ አይነቱ የመገናኛ ዘዴ ፍርድ ቤቶች ያደረጓቸውን ማሻሻያዎች በፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች አማካኝነት በቀጥታ በሚደረግ የጥያቄ እና የመልስ የመረጃ ልውውጥ ለማህበረሰቡ እንዲደርስ የሚያገለግል ነው። እንዲህ አይነቱ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ በተለይም ጎበዝ እና ንቁ የሆኑ ጋዜጠኞች ያልታተሙ የፍርድ ማሻሻያ ፕሮግራሞች የለውጥ ተግባራትን ከፍርድ ቤት ኃላፊ ለማግኘት የሚያስችላቸው ሲሆን በአንፃሩ የፍርድ ቤቱ ኃላፊ መተላለፍ የሚፈልገውን መረጃ

ለህብረተሰቡ እንዲደርስ እድል የሚፈጥሩት ቢሆንም ከንግግር እና ከቃላት አጠቃቀም ስህተት በፍርድ ቤቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ መረጃዎች ሊያስተላልፉ የሚችሉ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻው ዘዴ ነው፡፡

- **ድረ-ገጽ፡-** ፍርድ ቤቶች ከህዝብ ጋር ሊተዋወቁ የሚችሉበት የራሳቸው ድረ-ገፅ ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን በድረ-ገፅ ላይ ያሉትን መረጃዎች በተለያየ ጊዜ እንዲሻሻሉ እና እንደ አዲስ መረጃዎች እንዲጫኑ በማድረግ የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችንና የለውጥ ተግባራትን ለህብረተሰቡ ለማድረስ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ አይነቱ የመገናኛ ዘዴ በተለይም አሁን ባለንበት የበየነ መረብ መረጃ ግንኙነት (የኢንፎሜሽን ኮሙኒኬሽን) ዘመን የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ በድረ-ገፅ በኩል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ተግባር በተለይም ባለድርሻ አካላትንና ሙያቸው ከህግ ስራ ጋር የተያያዘ ሰዎችን እና ሲቪል ማህበራትንም ጭምር የፍ/ቤቱን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና የለውጥ ተግባራት በቀላሉ ለማግኘትና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያግዛቸው በመሆኑ የሚበረታታ የመገናኛ ዘዴ ነው ለማለት ይቻላል፡፡
- **የማህበራዊ ትስስር የመገናኛ ብዙሀን**፡- ይህ የመገናኛ ዘዴ አሁን ባለንበት ዘመን በተለይም አምራች ሀይል ተብሎ የሚታሰበው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የሚገለገልበት የመገናኛ ዘዴ አይነት ከመሆኑም በላይ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ፍርድ ቤቶች የሚያደረጉትን የማሻሻያ ስራዎች በቀጥታ ለህብረተሰቡ ለማድረስ የሚያስችላቸው ሲሆን በሚያደረጉት የመረጃ ልውውጥ ሁኔታ እና በማሻሻያው ፍሬ ጉዳይ ላይ በፍጥነት ከህብረተሰቡ ግብረ መልስ የሚያገኙበት ዘዴ ነው፡ በእርግጥ ይህ የመገናኛ ዘዴ ፍርድ ቤቶች ለህዝብ ለማድረስ የሚፈልጉትን መረጃ እጅግ በጣም በአጭሩ ለመግለፅ የሚያስገድዳቸው በመሆኑ የተሟላ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ መረጃ ለህብረተሰቡ ከማድረስ አንፃር ውስንነት ይኖረዋል፡፡
- **መረጃን በፊልም ቀረፃመልክ ማስተላለፍ**፡- እንዲህ ያለው ዘዴ የሚያገለግለው አንድ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራም ለጠቅላላ ማህበረሰቡ ወይም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ በማሰብ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የማድረጊያ መንገድ ሲሆን በፊልም መልክ እንዲቀረፅና ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የተፈለገው መረጃ በተደጋጋሚ በፍርድ ቤቶች የስራ ክፍሎች ከተገመገመና ከተስተካከለ በኃላ ህብረተሰቡ በቀላሉ በሚገነዘብበት እና አሰልቺ ባልሆነ አቀራረብ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ እንዲህ ያለው የመገናኛ መንገድ የሚዲያ ባለሙያዎችን አስተዋፅኦ የሚፈልግ በመሆኑ

በዚህ ረገድ ሙያው ያላቸው አካላት እንዲሳተፉበት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በፊልም መልክ የተቀረፀው መረጃ በፍርድ ቤቶች ድረገፅ (ዌብሳይት) ፣ በዩቲዩብ እና በቴሌቪዥን አማካኝነት ለህብረተሰቡ ሊተላፍ ይችላል፡፡ እዲህ አይቱ የመገናኛ ዘዴ ከፊልም ቀረፃው ጀምሮ የተቀረፀውን እስከማስተላለፍ ድረስ ያለው ስራ ከፍተኛ ሀብት የሚያስፈልገው ሲሆን ብዙ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን ተግባራት ከሌሎች ጋር በመተባበር ቢያደርጉት ይመከራል፡፡

- **የፍርድ ሂደትን በመገናኛ ብዙሀን ማስተላለፍ፡-** ይህ አይነት መረጃን የማስተላለፊያ መንገድ በተለይም በተመረጡ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ሲሆን በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ የሚደረገው የክስ እና የክርክር መሠማት ሂደት በቀጥታ በካሜራ እየተቀረፀ የሚተላለፍበት መንገድ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ የፍርድ ቤቶች የመስማት ሂደት በቀጥታ ስርዓት እየተላለፈ በሚገኝበት ወቅት ዳኞች፣ ጠበቆች፣ ዐቃቤ ሕጎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሀሳባቸውን በጉዳዩ ላይ እንዳይሰበስቡ የማድረግ አጋጣሚን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በወንጀል ጉዳይ ላይ የተከሳሹን ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት የሚጎዳ ፣ በፍ/ብሔር ጉዳይ የተከራካሪዎቹን መልካም ስምና ዝና ና ሚስጥር አደባባይ ላይ የሚወጡበትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ጥንቃቄ የሚያሻው የመገናኛ መንገድ ነው፡፡ ይህ የመገናኛ ዘዴ ተገቢነት እና ህጋዊነት በህግ ባለሙያውና ልሂቃን ዘንድ እጅግ አከራካሪ በመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው የአገሮቹ ህጎች በዚህ ረገድ ያስቀመጡት ድንጋጌ ታሳቢ ተደርጎ መሆን ይገባዋል፡፡

በአጠቃላይ ፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞቻቸውንና የለውጥ ተግባራቸውን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎና መንገዶች ለህብረተሰቡ ለማድረስ የሚችሉ እና የሚገባቸው ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት የመገናኛ ዘዴዎችና መንገዶች ብቸኛ ሳይሆኑ ከመገናኛ ዘዴዎችና መንገዶች የተወሰኑት በመሆኑ ፍርድ ቤቶች እነዚህንና ከየወቅቱ አንፃር የሚፈጠሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከህብረተሰባቸው ጋር አስፈላጊ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ የፍርድ ቤቶቹን ማሻሻያዎች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## <u>የመወያጥያቄ</u>

- ከላይ ከተገለጹት ስትራቴጅዎችና መንገዶች በተጨማሪ ሌሎች የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ የመረጃ ልውውጥ ስትራቴጅዎችና መንገዶች ካሉ ግለጽ?

# ምዕራፍ ሰባት፤

# የችሎት ውሎ ዘገባ

ፍርድ ቤቶች ችሎት ሲያስችሉ በግልጽ ችሎት መሆን እንደሚገባው አገራት በተለያዩ ህጎቻቸው ውስጥ ይደነግጋሉ። የዚህም ዓለማም የፍርድ ቤቶች ስራ ለህብረተሰቡ በግልፅ እንዲታይ ለማድረግ ሲሆን በተወሰኑ በህግ በተከለከሉ ጉዳዮች ወይም ዳኞች የጉዳዩንና የነገሩን ሁኔታ ተመልክተው ችሎቱ በዝግ እንዲካሄድ ትዕዛዝ ካልሰጡ በቀር ማንኛውም የፍርድ ስራ ሂደት በግልፅ ችሎት መካሄድ ይኖርበታል። በዚህም ምክንያት ማንኛውም ችሎት ለመከታተል የሚፈልግ የህብረተሰብ ክፍል ፍ/ቤቱ ችሎት የሚያስችልበት እና ሂደቱን ለመከታተል የሚያስችሉ የፍርድ ቤቱ መሰረተ ልማቶች እስካልገደቡ ድረስ የኩነቱ ታዳሚ ይሆናል።

እንደሚታወቀው የችሎት ውሉ የመገናኛ ብዙሀንና የአብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ትኩረት የሚስብ ጉዳይ ሲሆን በተለይም አንድ አንድ የወንጀል እና የፍትሀብሔር ጉዳዮች ላይ መገኘት ብዙሀን ለመዘገብ የተለየ ፍላጎት የሚያሳዩበቸው ሆነው ይታያሉ።

የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች የፍርድ ቤት ዘገባዎችን በመስራት ለህብረተሰቡ መረጃዉ እንዲደርስ ሲያደርጉ ህብረተሰቡ ከጉዳዩ በመማር የፍትህ አጋዥ እንዲሆን ያስችላል፤ ፍርድ ቤቶች በችሎት አመራር እና በፍትህ አሰጣጥ ላይ ያደረጉትን ማሻሻያ ህብረተሰቡ እንዲገነዘበው ያደርጋል። ከዳኞች ተጠያቂነት አንፃር የራሱን ሚና ይጫወታል ፤ እንዲሁም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሙያቸው የሚፈቅድላቸውና እውቀቱ ያላቸው ሰዎች ከችሎት ውሎ ዘገባው በመነሳት በዛው በተለየው ጉዳይ ላይ ወይም ለችሎት ውሎ ዘገባዉ መነሻ በሆነው መዝገብ ላይ ተግባራዊ በተደረገው ህግ ወይም ማስረጃ ምዘና ላይ መሰረት በማድረግ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊሰሩ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶቹ ጉዳዩን በሚመለከት በተከተሉት የስነ ምግባር ሁኔታ ላይ የምርምር እና ጥናት ስራ ለመስራት እንዲችሉ እድል ይፈጥራል።

የችሎት ውሎ ዘገባ በአግባቡና ስነ ምግባርን በተላበሰ ሁኔታ ከተዘገበ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች የሚያስገኝ እንደመሆኑ መጠን በአንፃሩ የመገናኛ ብዙሀን የፍርድ ሂደቱን ባልተገባ ሁኔታ የሚዘግቡት ከሆነ የሚያደርሰው ጉዳት እጅግ ከባድ ከመሆኑም በላይ የማይመለስና የማይተካ ያደርገዋል። የችሎቱ ውሎ ዘገባ በአንድ በኩል ፍርድ ቤቶች ስራቸውን በግልጽ ችሎት ማካሄድ ይኖርባቸዋል የሚለውን መርህ

ለማሳካት የሚያስችል ሲሆን ይህን ግብ ለማድረስ ሲሰራ ግን  የተከሳሽን፣ የተከራካሪ ወገኖችን ፣የፍርድ ቤት ዳኞችን እንዲሁም የፍርድ ቤቱን መብቶችና ነፃነት መንካት አይኖርበትም።

የትኛውም የችሎት ውሎ ዘገባ በወንጀል ጉዳይ ተከሶ የቀረበን ሰው ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት ንፁህ ሆኖ የመገመት መብቱን  በምንም አይነት አኳኋን የሚነካ ከሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በፍትሐብሔር ጉዳይም ቢሆን ጥብቅ የሆነ የንግድ ሚስጥር እና መልካም ዝናን የሚመለከት ጉዳዮች ክርክር በሚደረግበት ወቅት ይህንኑ ሁኔታ የተከራካሪዎቹን መብት በሚጎዳ አኳኋን መዘገብና ለህብረተሰቡ ማሰራጨት በእነዚሁ ተከራካሪዎች ላይ ከሚያመጣው የመብት መጣስና እና ኪሳራ ባሻገር በተመሳሳይ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የውጭ አገር ባሀብቶች (ኢንቨስተሮች) በሁኔታው በመደናገጥ ወደ ሌሎች ህጋዊ ያልሆኑ አማራጮች የማምራትና ከአገርም የመዉጣት ውሳኔን የሚያስተላልፍበት እድል ስለሚኖር የችሎት ውሎ ዘገባ መልካም የሆነ ማህበራዊ ጥቅም እንደሚያስገኘዉ ሁሉ በአግባቡ ካልተመራና ካልተያዘ እጅግ የከፋ ጉዳት የሚያስከትል ተግባር ነው።

ከዚህ አንፃር ፍርድ ቤቶች የችሎት ውሎ ዘገባዎች ሲሰሩ የሚያመጡትን ጉዳት ለማስወገድ ወይም ጉዳቱን ለመቀነስ እንዲቻል የራሳቸውን ሚና በመለየትና አቅጣጫ በማስቀመጥ እንዲሁም ለተግባራዊ ተፈፃሚነቱ ከፍተኛ ሃላፊነት በመውሰድ ሊሰሩ ይገባቸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የመገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች የችሎት ውሎ ዘገባዎችን በሚሠሩበት ጊዜ ዓላማቸው መረጃ ለህብረሰቡ በትክክል ተላልፎ በማህበረሰቡ አኗኗር ላይ በጎ ተፅዕኖ እንዲያሳርፍ ማስቻል ይኖርበታል። በመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 55 ድንጋጌ መሰረት በፕሮግራም ስርጭቱ ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ የሚያደርግ፣ ለሰብዓዊ መብትና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መጠናከርና መጎልበት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የችሎት ውሎ ዘገባዎችንና ፕሮግራሞችን ማበረታታት እንደሚያስፈልግ አከራካሪ አይሆንም።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚመለከቱ የወንጀል ጉዳይ ዘገባዎችን በተመለከተ ከአዘጋገባቸው ጀምሮ የሚሰራጩበትንም መንገድ ከጊዜ እና ከሁኔታ ጋር አመዛዝኖ ማሰራጨት ያስፈልጋል። [53] ሃይማኖትና ብሔርን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮችን የሚመለከት የችሎት ውሎ ዘገባ በሃይማኖት ተከታዮች

[53] የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013ዓ.ም አንቀጽ 69

መካከል እርስ በእርስ ግጭት በሚያነሳሳ ፤ የተወሰኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ሀይማኖት ወይም እምነት በሚያንኳስስ ፤ ወይም በሀይማኖት ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር በሚያስችል አኳኋን መዘገብ የማይኖርበት በመሆኑ የመገናኛ ብዙሀን ይህንኑ የህግ ኃላፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ፣ የችሎት ውሎ ዘገባ የሚሠሩ ጋዜጠኞችን በዚሁ አግባብ በማዘጋጀት የዘገባ እና የማሰራጨት ስራውን ሊሰሩ ይገባል። [54]

**ጥያቄ**

- የችሎት ውሎ ዘገባዎች ከፍርድ ቤቶች ነጻነት እና ተጠያቂነት አንጻር የሚኖራቸውን ፋይዳ በዝርዘር አስረዳ? (4 ደቂቃ)

- የችሎት ውሎ ዘገባፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ እንዲጨምር ከማድረግ አንጻር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ካለ በትክክል በመግለጽ በዝርዝር አስረዳ? (4 ደቂቃ)

## 7.1. መልካም የችሎት ውሎ ዘገባ እንዲኖር ምን ይደረግ?

መገናኛ ብዙሀን የችሎት ውሎ ዘገባ በሚያከናውኑበት ወቅት በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህጎችና የስነ ምግባር ደንቦች አክብረው መስራት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ከሌሎች የመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ጭምር ይህንኑ ስራ ለሚሠሩ ጋዜጠኞች ስልጠና መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ለጋዜጠኞች እና በማሰራጨት ሙያ ላይ ለተሰማሩ አባላቶቻቸው ስልጠና ከመስጠት ባሻገር በየጊዜው በሚደረግ ግምገማ ጋዜጠኛውንና ሌሎች ደጋፊ ሠራተኞች ስልጠናውን በተገቢው ያገኙና የተገነዘቡ መሆኑን መከታተል፤ ይህንንም የሚያረጋግጥ የመከታተያ ስርዓት መዘርጋትና ተፈፃሚ ማድረግ።

የችሎት ውሎ ዘገባዎች ለህዝብ ከተሰራጩ በኋላ ያመጡትን መልካም ተፅዕኖና ያደረሱትን ያልገተባ የአመለካከት ዝንባሌ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤ በአንድም ሆነ በሌላ ዘዴ በመጠቀም ህብረተሰቡ በችሎት ውሎ ዘገባዎች ላይ ያለውን አስተያየት በማወቅ ህብረተሰቡን አሳታፊ የሚያደርጉ አውዶችን እየፈጠሩ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ።

---

[54] የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013ዓ.ም አንቀጽ 70

የችሎት ውሎ ዘገባ ሲሰራ በተሟላ ሁኔታና በችሎት ውስጥ የነበረውን የሁሉንም ወገኖች ሀሳብ በማካተት ያለ ምንም ተጨማሪ ሀሰተኛ ቃል መሰራት የሚገባው ቢሆንም አንዳድ ጊዜ የህግ አነጋገሮችና ቃላት ካላቸው ልዩ ባህሪ ፤ፍርድ ቤቶች የሚሠሩባቸው የስነ-ሥርዓት ህጎች ውስብስብ መሆንና ፤ ከጋዜጠኛው ያልተገባ ድርጊት ጭምር የተሳሳተ ዘገባ ሊሰራ የሚችልበት እድል በመኖሩ በመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 4 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች መሰረት የተሳሳተ መረጃው የተሰራጨበትን አድማስ የሚመጥን የእርማት ዘገባ ማካሄድ።

የመገናኛ ብዙሀን በሚፈጥሩት የእርስ በእርስ ቁጥጥር መድረክ የችሎት ውሎ ዘገባን በሚመለከት መገናኛ ብዙሀኖች የሰሯቸውን ስራዎች ለግምገማ በማቅረብ ዘገባው የሙያ ስነ ምግባር፣ የሰብዓዊ መብቶች እና የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ዉስጥ ባስገባ አኳኋን መሰራት አለመሰራቱ በማረጋገጥ ውስንነት ካለም ይህንኑ እንዲያስተካክል እርስ በእርስ በመተራረም የችሎት ውሎ ዘገባን ጥራት በሀገራችን ስር የሰደደና የተሻለ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።[55]

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ልዩ የህዝብ ብሮድካስት አገልግሎት መመስረት የሚችሉ ሲሆን ስራቸውን የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃዎችና የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ያደረጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጥ የመገናኛ ብዙሀን ከመሠረቱ ከላይ የተገለፁትን የመገናኛ ብዙሀን መገናኛ ተቋማት ሊተገብራቸው የሚገቡ ተግባራትን በመተግባር የችሎት ውሎ ዘገባዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላሉ።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የችሎት ውሎ ዘገባ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉበትን ደረጃ በባለሙያዎች በማስጠናት ችግሮችን በመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ረገድ የሚሠሩ ጥናቶችን በመደገፍ፤ የጥናት ፅሁፎች እንዲኖሩ በማድረግ የችሎት ውሎ ዘገባ የጥራት ደረጃ እንዲሻሻል ለማድረግ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም የመገናኛ ብዙሀን መገናኛ ተቋማትና የፍርድ ቤት የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የችሎት ውሎን ዓላማ እና የአዘጋገብ ሁኔታን የሚመለከት ስልጠና በመስጠት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

ፍርድ ቤቶች የችሎት ውሎ ዘገባ ጥራትን ለማሻሻል ስለ ፍርድ ሂደት እና በፍርድ የተጠናቀቀን ጉዳይ አዘጋገብ በተመለከተ ከፍርድ ቤቶች ነፃነትና ገለልተኛነት እንዲሁም ከተከራካሪ ወገኖች የሰብዓዊ መብቶች

---

[55] የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013ዓ.ም አንቀጽ 2(34)

አንፃር እንዴት መዘገብ እንደሚገባው የመገናኛ ብዙሀን አዋጅን፣ ህገ መንግስቱን የአለምአቀፍ ስምምነቶችን ድንጋጌዎች እና መስፈርቶች እንዲሁም ሌሎች ህጎችን መሠረት በማድረግ ተደጋጋሚና ውጤታማ የሆኑ ስልጠናዎችን ለመገናኛ ብዙሀን ተቋማትና ለጋዜጠኞች ስልጠና በመስጠት የችሎት ውሎ ዘገባን እንዲሻሻል አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

ችሎት የሚያስችሉ ዳኞች የችሎት ውሎ ዘገባ የሚሠሩ የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች በችሎት መገኝታቸውን ካረጋገጡ ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት የችሎት ውሎው አዘጋገብ ምን መሆን እንደሚገባው አጭር ገለፃ በማድረግ አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች መሪነት የሚቋቋም የባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ኮሚቴ በማዋቀር የችሎት ውሉ ዘገባዎች ያሉበትን ደረጃ እና መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች በመገምገም ለፍርድ ቤቶች ለመገናኛ ብዙሀን ተቋማትና እና ለባለድርሻ አካላት ሪፖርት እንዲደርስ በማድረግ የሚኖሩትን ለውጦች በሚገባ ለማሻሻል የተገኙ ውስንነቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል ውሳኔ እንዲተላለፍ በማድረግ የችሎት ውሉ ዘገባ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቶች የችሎት ውሎ ዘገባዎች ለማህበረሰቡ ከተላለፉ በኋላ በተለይም ንፁህ ሆኖ ከመገመት መርህ፣ ከስም ማጥፋት ተግባር እንዲሁም ከአጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች አለመከበር እና ከፍርድ ቤት ነጻነትና ገለልተኛነት አንፃር ጉድለት ያለባቸዉ የችሎት ውሎ ዘገባዎች በታዩ ጊዜ በተከራካሪ ወገኖች በሚቀርብለት አቤቱታ ወይም ችሎቱ በራሱ አነሳሽነት ዘገባውን ያከናወነውን ተቋምና ጋዜጠኛ በመጥራት አስፈላጊውን የማስተማሪያ እርምጃ ሊወስድ የሚገባ ሲሆን ፍርድ ቤት እንደተቋም ከመገናኛ ብዙሀን ተቋማትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ በማድረግ የችሎት ውሎ ዘገባዎች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ይችላሉ፡፡

**ጥያቄ**

- መልካም የችሎት ዉሎ ዘገባ አለመኖር በፍርድ ቤቶች ላይ የሚያመጣዉ አሉታዊ ተጽዕኖ ካለ በዝርዝር አስረዳ? (5 ደቂቃ)

## መደምደሚያ እና መፍትሄ ሀሳቦች

በኢትዮጵያ ውስጥ በየዘመኑና በተለይም የመንግስት ስርዓት ለውጥ በተደረገ ቁጥር የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራት እንደ አንድ አጀንዳ እየተነሳ በተቻለ መጠን የለውጥ ተግባራት ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራሞች በፍርድ ቤቶቹ በራሳቸው ችግር እንዲሁም ህግ አስፈጻሚው የመንግስት አካል በሚያሳርፈው አሉታዊ የጣልቃ ገብነት እና የቁጥጥር ድርጊቶች እንዲሁም ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቶች ተግባራት ላይ ያለው የንቃተ ህሊና ማነስ ተደማምረው በሚፈለገው ደረጃ የህዝብ አመኔታን የተጎናጸፉ፣ ስራቸውን በዘመናዊ እና ሰብአዓዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ የሚሰሩ ፍርድ ቤቶችን የመፍጠር ሂደት ከፍተኛ ውስንነት ያለበትና እስከ አሁንም ያልተሻገርነው ጉዳይ ነው፡፡

የፍርድ ቤቶች የማሻሻያ ተግባራት በሚፈለገው ደረጃ አለመፈጸም ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የታዩ እና እየታዩ ያሉ መልካም የማሻሻያ ተግባራት ጅማሬዎች በሚገባ ለህበረተሰቡ እንዲተዋወቁ አለመደረጉ ህዝቡ ፍርድ ቤቶችን የመጨረሻ የመብት ማስከበሪያ እና የግዴታዎች ማስፈጸሚያ አድረጎ የመውሰድ ዝንባሌው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አድርሷል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች የቀረጿቸውን ፕሮግራሞች ወደ መደበኛ ስራነት መቀየራቸው ወሳኝ እንደ ሆነ ሁሉ የተሰሩ ስራዎችን እና ያጋጠሙ ችግሮችን ለህዝብ ማድረስ እና የመረጃ ልውውጥ ስራ መስራት አለባቸው፡፡

የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያዎች ለህዝብ ማስተዋወቅ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን በተለይም የፍርድ ቤቶችን አመኔታ እንዲሻሻል በማድረግ፣ ፍርድ ቤቶቹ የሚያነሷቸዉን ጥቅሞችና መብቶች በማስከበር ረገድ ያለው ሚና እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን በጀትና የሰው ሀይል በመመደብ ፍርድ ቤቶች የሚሰሯቸውን ስራዎች ለህዝብ ማድረስ ይኖርባቸዋል፡፡

የፍርድ ቤቶችን የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ተግባራትን የሚመለከቱ የመረጃ ልውውጥ ስራዎች በአንድ አካል ልፋት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ ብዙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡ ከእነዚህም ባለድርሻ አካላት መካከል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣የሚዲያ ተቋማት ሚና የጎላ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች የመረጃ ልውውጥ ተግባራትን በማገዝ ረገድ የትኞቹ ባለድርሻ አካለት ተሳትፎ ከፍተኛ ነው የሚለውን በመለየት፤ ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ፤

ስራዎችን በመከፋፈልና፤ከስራዉ በኋላ ግምገማዎችን በማድረግ ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ ተግባራትን መፈጸም ይገባቸዋል፡፡

የመረጃ ልውውጥ ተግባርን በተቀላጠፈና በሚፈለገው ደረጃ ለማካሄድ በቅድሚያ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መለየት የሚያስፈልግ ሲሆን እነዚህኑ ችግሮች ታሳቢ በማድረግ ከየፍርድ ቤቶቹ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በመተርጎም የህዝብ ግንኙነት እቅድ መንደፍ ያስፈልጋል፤ ከዚህ በተጨማሪ መልካም የሆነ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ፍርድ ቤቶች ባለድርሻ አካላትን ያቀፈና ራሱን የቻለ መመሪያ ያለው ማንዋል በማዘጋጀትና መገናኛ መድረክ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፍርድ ቤቶችን የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችና የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ጋዜጠኞችን የህግ እውቀት ለማሻሻል የሚረዱ ተደጋጋሚ ስልጠናዎችን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ማዘጋጀት ይገባል፡፡

የመረጃ ልውውጥ ተግባሩም መመራት የሚገባው እንዲሁ በዘፈቀደ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሌሎች ባለድርሻ አካለትን ባሳተፈ ሁኔታ የፍርድ ቤቶችን ማሻሻያ ለማሳወቅ የሚረዳ ስትራቴጅ መቅረጽ ይጠበቅባቸዋል፤ በአገሪቱ ዉስጥ ያሉትን እና አዳዲስ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የመገናኛ መንገዶች እና ዘዴዎችን ጥቅምና ጉዳት በመለየትና በመተንተን ጥቅም ላይ መዋል ይገባቸዋል፡፡

# ዋቢ መጽሀፍት


- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ  ህገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987
- በተሻሻለዉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት  የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ቁጥር 52/1958
- የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1997
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 185/1954
- የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1234/2013
- ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት
- ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት
- ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት
- ሁሉን አቀፍ የሰብኣዊ መብቶች መግለጫ
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስትም አቅም ግንባታ ሚኒስቴር፣የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም የጥናት መነሻ ሪፖርት፣ 1998ዓ.ም
- የፌደራል የፍትህና የህግ ምርምር እና ስልጠና ኢንስቲትዩት፣የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም በፌደራል ተቋማት ያለበትን ደረጃ ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት፣2011ዓ.ም.
- የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዳኝነት አካሉ አሁናዊ ሁኔታና የወደፊት እይታ፣ታህሳስ 2012
- የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣የስልጠና ሞጁል
- አሰፋ ፍሰሀ፣ፌደራሊዝም እና ልዩነትን ማቻቻል በኢትዮጵያ፡የንጽጽር ጥናት (ኔዘርላንድስ፣ዎልፍ የህግ አሳታሚዎች፣እ.ኢ.አ. 1997ዓ.ም
- ሄነሪ ስኮለር፣የኢትዮጵያ የህገ መንግስትና የህግ እድገት፡ ኢትዮጵ ህገ መንግት እድገት ላይ የተሰራ ጥናት ቮሊዩም I ፣ እ.ኢ.አ.1997 ዓ.ም
- ሮበርት አለን ሴድለር፣የኢትዮጵያ የስነ ስርዓት ህግ፣ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አታሚ፣1968
- ፍርድ ቤቶችና የአቃቢ ህግ ባለስልጣናት ለመገናኛ ብዙሀን እና ለህዝቡ የመረጃ ልዉዉጥ ማከናወኛ መመሪያ፣31ኛዉ ሲኢፒኢጀ ቋሚ ስብሰባ ታህሳስ 3 እና 4፣ 2018፣ስትራስበርግ
- Canadian Judicial Council. (1998). Ethical Principles for Judges. Ottawa, Ontario: Canadian Council Ministry of Capacity Building. (2002).

- Justice System Reform in Ethiopia: Proceeding of the Work Shop on Ethiopian's Justice Reform, Addis Ababa: MCB
- Shetreet, Shimon, and Jules Deschens, (eds.,) (1985). Judicial Independence: The Contemporary Debate, Dordrecht: Martinus Nijhoff Publishers.or Martinus Nijhoff Publishers, Boston/Lancaster.
- Muga Dorcas Anyang, The Role Of Public Relations in Building the Image Of the Keneyan Judicial System, A Research project submitted in partial fulfilment of the requirement for the award of the degree of Master of Arts in Communication Studies at the School of Journalism and Mass Communication, University of Nairobi. November 2012.
- Elias N. Stebek (2016), Assessment of Ethiopia's Justice Sector Reform Components in GTP I and GTP II, Ethiopian Lawyers Association and Ethiopian Young Lawyers Association, Addis Ababa, Ethiopia